# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 070 ኅዳር 10 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# «ቀይ ባሕር የኢትዮጵያ እስትንፋስ ነው»

- ፕሮፌሰር አድማሱ ገበየሁ
በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የውሃ ሳይንስ ተመራማሪ

**ተስፋ ፈሩ**



አዲስ አበባ፡- ቀይ ባህር ከኢትዮጵያ ደህንነት፣ ልማትና ገናናነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ለኢትዮጵያ የእስትንፋስ ያህል ወሳኝነት አለው ሲሉ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የውሃ ሳይንስ ተመራማሪው ፕሮፌሰር አድማሱ ገበየሁ ገለጹ።

ፕሮፌሰር አድማሱ ገበየሁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ደህንነት ከቀጣናው ጋር የተያያዘ በመሆኑ ልማቷም ሆነ ጥፋቷ በቀይ ባህር ሁኔታ የሚወሰን ነው።

ከቀይ ባህር እንራቅ ብንል እንኳን ምን ጊዜም መዘዙ ሊለቀን አይችልም ያሉት ተመራማሪው፤ በቀይ ባህር ጉዳይ አርፈን እንቀመጥ የሚባል ነገር ሊኖር እንደማይችል ጠቁመዋል።

የባህር በር ጉዳይ ከሚያሳስባቸው ሰዎች አንዱ እንደሆኑ የገለጹት ፕሮፌሰሩ "በአጠቃላይ ቀይ ባህር ውስጥ ያለው ሁኔታ ይመለከተናል፤ የቀይ ባህር ጉዳይ የሚመለከተን ወደብ ለማግኘት ብቻ አይደለም" ብለዋል።

ቀይ ባህር ኢትዮጵያ ከተቀረው ዓለም ጋር በኢኮኖሚ የምትተሳሰርበት በር እና እስትንፋስ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ለቀይ ባህር በመልከዓ ምድር ቅርብ


**"ቀይ ባህር ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል**


## የአየር መንገዱ የከፍታ ጉዞ

**ተስፋ ፈሩ**



የኢትዮጵያ አየር መንገድ የኢትዮጵያ ስም በመላው ዓለም በበጎ እንዲነሳ በማድረግ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ተቋም ሆኗል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአሁኑ ወቅት የ20 "ኤ350-900 ኤር ባስ" አውሮፕላኖች ባለቤት ሲሆን፤ ዱባይ በተካሄደው የ2023 የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ ዓውደ ርዕይ ላይ በአንድ ሳምንት ውስጥ 78 አውሮፕላኖችን ለመግዛት ከአሜሪካዎቹ ቦይንግ እና ኤር ባስ ኩባንያዎች ጋር ስምምነት ፈጽሟል።

አየር መንገዱ ከኤር ባስ ኩባንያ ጋር ባደረገው ስምምነት 11 "ኤርባስ ኤ350-900ኤስ" አውሮፕላኖች ለመግዛት ተፈራርሟል። ስምምነቱ እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ስድስት አውሮፕላኖችን ማዘዝ የሚያስችል ዕድል የተካተተበት ነው። "ኤ350 ኤር ባስ" አውሮፕላን ዘመናዊ እና ቀልጣፋ ሰፊ ሰው ጫኝ እና ከ300 እስከ 410 መቀመጫዎች ያለው የረጅም ርቀት አውሮፕላን ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቦይንግ ኩባንያ ጋር ባሰረው ውል 67 አውሮፕላኖችን ለመግዛት ተስማምቷል። ግዢው 11 "787 ድሪምላይነር" እና 20 "737 ማክስ" አውሮፕላኖችን እንዲሁም 36 ሌሎች አውሮፕላኖችን የሚያካትት ነው።

አውሮፕላኖቹ በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ አየር መንገዱ እጅ ይገባሉ ተብሎ ይጠበቃል። አዳዲሶቹ አውሮፕላኖች የተሻሻሉ ሞዴሎች መሆናቸውና በውጤታማ የነዳጅ አጠቃቀማቸው ከቀደሙት አውሮፕላኖች አንጻር 20 በመቶ የበካይ ጋዞችን ልቀት


**የአየር መንገዱ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል**


## የኢትዮጵያ ምርት ገበያ

### የጉሎ ፍሬ፣ ተልባና ጤፍ ሊያገበያይ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት ተልባ፣ የጉሎ ፍሬ እና ጤፍ በዘመናዊ ግብይት ሥርዓት ለማገበያየት በዝግጅት ላይ መሆኑን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገበያና ግብይት ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ በኃይሉ ንጉሤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ምርት ገበያ በተያዘው በጀት ዓመት ተልባ፣ የጉሎ ፍሬ እና ጤፍ በዘመናዊ ግብይት ሥርዓት ለማገበያየት በዝግጅት ላይ ነው። የተልባና የቢራ ገብስ ጥናት ተጠናቆ ለማኔጅመንት ቀርቧል።

ምርቶቹ በሀገር ውስጥ ገበያ ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድሩ


**የኢትዮጵያ ምርት... ወደ ገጽ 6 ዞሯል**




አቶ በኃይሉ ንጉሤ

## ኢትዮጵያን በሰው ሠራሽ አስተውሎት

### ዘርፍ ከአፍሪካ ቀዳሚ ለማድረግ እየተሠራ ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡-ኢትዮጵያን በሰው ሠራሽ አስተውሎት (አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ) ዘርፍ ከአፍሪካ ግንባር ቀደም የሚያደርጋትን ተቋም እውን ለማድረግ እየተሠራ ነው ሲል የኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት አስታወቀ ።

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ወርቁ ጋቸና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢንስቲትዩቱ ከተቋቋመ ሶስት ዓመታትን አስቆጥሯል።


**ኢትዮጵያን በሰው ሠራሽ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል**

















ዜና

# ባለሥልጣኑ አሮጌ መኪና ያላቸው አሽከርካሪዎች

## አስቀድመው መፍትሄ እንዲያዘጋጁ አሳሰበ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በመዲናዋ ከፍተኛ ጭስ የሚለቅ መኪና ያላቸው አሽከርካሪዎች አስቀድመው መፍትሄ እንዲያዘጋጁ የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አስታወቀ። የመኪና ጭስ ስታንዳርድ እየተዘጋጀ መሆኑንም ተገልጿል።

የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ድዳ ድሪባ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤የመኪና ጭስ ስታንዳር እየተዘጋጀ ነው። በዚህም እያንዳንዱ መኪና የሚያስወጣው ጪስ የሚለካ ይሆናል።

መኪናው ከተቀመጠው መለኪያ በላይ ጪስ የሚያመነጭ ከሆነ አገልግሎት እንዳይሰጥ ይደረጋል ብለዋል።

አብዛኛውን ጊዜ ከፍተኛ ጭስ የሚለቁ ተሸከርካሪዎች ከተመረቱ 23 ዓመትና ከዚያ በላይ ያገለገሉ ናቸው ያሉት ኃላፊው፤ ስለዚህ አሮጌ መኪና ያላቸው አሽከርካሪዎች ከአሁኑ መፍትሄ ሊያዘጋጁ ይገባል ብለዋል።

በመዲናዋ አሮጌና ከፍተኛ ጭስ የሚለቁ በርካታ መኪኖች መኖራቸውን በመጥቀስ፤ መኪናዎቹን



አቶ ድዳ ድሪባ

በአንድ ጊዜ ሥራ እንዲያቆሙ ማድረግ እንደማይቻል አመላክተዋል፡፡

ሆኖም ቦሎ የሚሰጡ፣ መኪናዎችን የሚቆጣጠሩና መኪና የሚገዙ አካላት ባለሥልጣኑ የሚያወጣውን የጭስ ስታንዳርድ መሠረት እንዲያደርጉአቶ ድዳ አሳስበዋል።

እንደ ኃላፊው ገለፃ፤ ስታንዳርዱ በቅርቡ ተግባራዊ ይደረጋል። ስለዚህ አሮጌና ከፍተኛ ጭስ የሚለቅ መኪና ያላቸው አሽከርካሪዎች ጭስ የሚቀንስ ቴክኖሎጂን መጠቀም ወይም መኪናውን መቀየር ይኖርባቸዋል።

አገልግሎት የሰጡ መኪናዎች እንደበፊቱ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ቢደረግ ኖሮ አዳዲስ መኪናዎች ወደ ከተማዋ አይገቡም ነበር ያሉት አቶ ድዳ፤ እየተዘጋጀ ያለው የመኪና ጭስ ስታንዳርድ ለአየር መበከል አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ጋዞችና ብናኞች ጋር ተያይዘው የሚመጡ የጤና ችግሮችን ለመቀነስ ያስችላል ብለዋል።

በመዲናዋ የአየር ጥራት ለመቆጣጠር የሚያስችሉ 10 ዘመናዊ መሣሪያዎች የተገጠሙ ሲሆን በቅርቡ ደግሞ ከመኪና የሚወጣውን ጭስ መቆጣጠር የሚያስችል መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

የአየር ጥራት መረጃ በተለይ በተገቢው ጊዜና ቦታ መረጃ መስጠት የአየር ብክለትን ተጋላጭነትን ለመቀነስ ወሳኝ ሚና አለው ብለዋል።

በዓለም የጤና ድርጅት በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ሀገራት የአየር ጥራት ስታንዳርድ ያዘጋጃሉ። አዲስ አበባም ይህን መሠረት ስታንዳርዶች እያዘጋጀች ነው ያሉት አቶ ድዳ፤ ይህም ለጤና ተስማሚ የሆነ አየር ጥራት እንዲኖር እንደሚያስችል ገልጸዋል።

# የኢትዮጵያ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት የሥራ ዕድል ፈጠራውን

## መረጃ መር እንዲሆን ያስችላል

- **በሥርዓቱ ከ400 ሺህ በላይ ዜጎች ተመዝግበዋል**

**ቃልኪዳን አሳዬ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የኢትዮጵያ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት የሥራ ዕድል ፈጠራውን እውቀትና መረጃ መር እንዲሆን ያስችላል ሲሉ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚል ገለጹ፡፡ በዚህ ሥርዓት እስካሁን ከ400 ሺህ በላይ ዜጎች መመዝገብ መቻሉን ጠቁመዋል፡፡

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ከክልል የዘርፍ ተቋማት አመራሮች ጋር ባደረገው የ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም የግምገማ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚል እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት የሥራ ዕድል ፈጠራውን እውቀትና መረጃ መር በሆነ መንገድ ትክክለኛ ውሳኔን ለመስጠት የሚያስችል ነው፡፡

በሂደቱ ውስጥ የሚያልፉ ጉዳዮች ከእጅ ንክኪ ነጻ እንዲሆኑ የሚያስችል በመሆኑ በዘርፉ ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጣ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በየአካባቢው የሚገኙ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ላይ ሥራ ፈላጊዎችም ሆኑ በሥራ ላይ የሚገኙ ዜጎችን በኢትዮጵያ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት የመመዝገብ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ያነሱት ወይዘሮ ሙፍሪያት፤ ይህ ምዝገባም ድግግሞሽን እንዲያስቀር በቴክኖሎጂ በመታገዝ የዜጎችን የእጅ፣ የፊትና የዓይን ዐሻራ በመውሰድ በመከናወን ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡

በዚህ ሥርዓትም እስካሁን ባለው ጊዜ ከ400 ሺህ በላይ ዜጎች ተመዝግበዋል፤ ካሉት ሁለት ሺህ 200 ማዕከላት ውስጥ አንድ ሺህ ማዕከላት የዚህ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ተደርገዋል፡፡

በተጨማሪም 400 ማዕከላት ወደ ሥራ ማስገባት መቻሉንና የተቀሩ 600 ማዕከላትን ደግሞ ወደ ሥራ ለማስገባት እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን አውስተዋል፡፡

ሥርዓቱ ለውጭ ሀገራት የሥራ ስምሪት የዜጎችን ደህንነት ለማስጠበቅ ትልቅ ድርሻ ያለው መሆኑን አንስተው፤ በሀገር ውስጥ ለሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች ለዜጎች የመሥሪያ ቦታ፣ ሥልጠናና ብድር ለማመቻቸት ወሳኝ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡



ወ/ሮ ሙፈሪሃት ካሚል

በተያዘው በጀት ዓመት ከሰኔ ወር ጀምሮ ልዩ ክህሎት መር የሆነ የሥራ እድል መፍጠሪያ እቅድ ተዘጋጅቶ ከፍተኛ ረብርብ ሲደረግ ቆይቷል፤ በዚህ የአምስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለአንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን ተናግረዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ሙፈሪያት ገለጻ፤ ይህ የሥራ ዕድል ፈጠራ ቋሚ የሚባሉ የሥራ ዕድል ፈጠራዎችን ብቻ ነው የሚያካትተው፡፡ የሥራ ዕድሉ ቋሚ ነው ለማለት ሶስት ወርና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ደሞዝ የሚከፈላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ መረጃዎችን የማጥራቱ ሥራ ባለማቋረጥ እየተሠራ ነው፡፡

በዚህም በሥራ ዕድል ፈጠራው ረገድ ከየአካባቢው የሚመነጩ ሪፖርቶችን የተዓማኒነት ደረጃ ለማረጋገጥ ጥናቶች እየተሠሩ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትሯ፤ የጥናቱ ግኝት እንደሚያመለክተው ባለፉት ሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ የተሠራው ሥራ 15 በመቶው ውድቅ የሚሆንና 85 በመቶው ለእውነት የተጠጋ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል ሲሉ ገልጸዋል፡፡



ካሳ ሚካኤል (ዶ/ር)

# የትምህርት ጥራትን

## ለማሻሻል የመምህራን የሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብሮችን ትኩረት መስጠት ይገባል

**አመለወርቅ ከበደ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የትምህርት ጥራትን ለማሳደግ ለመምህራን የሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብሮች ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ተገለጸ።

የአዲስ አበባ ትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን ያስጠናውና የመምህራን ተከታታይነት የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ፕሮግራም ጥናት ይፋ ተደርጓል።

ጥናቱን ያቀረቡት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሥነ-ትምህርት ኮሌጅ መምህርና ተመራማሪ ካሳ ሚካኤል (ዶ/ር)፤ በ414 የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ላይ እንዲሁም የ69 የትምህርት ቤት አመራሮች ላይ ጥናት መደረጉን አስታውቀዋል።

በጥናቱ መሠረት ጥራት ያለው ተከታታይ የመምህራን ሙያ ማሻሻያ ሥልጠና እየተሰጠ አለመሆኑን መገንዘብ ተችሏል ያሉት ዶክተር ካሳ፤ በዓመት 60 ሰዓት የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና መውሰድ የነበረባቸው መምህራን በተገቢው መንገድ ሥልጠናውን እየወሰዱ አለመሆኑ ተረጋግጧል ብለዋል።

ተከታታይ የመምህራን ሙያ ማሻሻያ ሥልጠና በ2001 ዓ.ም የተጀመረ ቢሆንም፤ ከውጤታማነት አንጻር ዝቅተኛ አፈጻጸም መታየቱን አስረድተዋል።

ከሥልጠናው ጋር ተያይዞ በመምህራን ዘንድ የአመለካከት ክፍተት መኖሩ በጥናቱ መታየቱን ገልጸው፤ በሥልጠናው ዙሪያ በቂ ቁጥጥር እንደማይደረግ አመላክተዋል።

የትምህርት አመራሩ በተከታታይ የመምህራን ሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ላይ የሚያደርገው ክትትል አነስተኛ መሆኑን ዶክተር ካሳ ተናግረዋል።

ተመራማሪው እንዳነሱት፤ በአሁኑ ወቅት በርካታ ቴክኖሎጂዎች እያደጉ እንደመሆናቸው መምህራን የትምህርት ጥራቱ ላይ ይበልጥ ያላቸውን አስተዋጽኦ ለማጉላት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል።

የአዲስ አበባ ትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን ሥራ አስኪያጅ አቶ ዳኛው ገብሩ በበኩላቸው፤ በትምህርት ሥርዓቱ የተማሪዎች ውጤት ለማሳደግ የማይተካ ያላቸውን መምህራን ብቃትና ጥራት ማሻሻል ተገቢ ነው ብለዋል።

አሁን ላይ የመምህራን ሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ላይ ያለውን ችግር ለመረዳትና የመፍትሄ አቅጣጫ ለማስቀመጥ በሚል በተከናወነ ጥናት መሠረት የተለዩ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ይደረጋል ሲሉ አመላክተዋል።

ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ መርሃ-ግብር ሲዘረጋ መምህራን ክፍተቶቻቸውን እያዩ እርስ በርስ እየተነጋገሩ ሙያቸውን እያጎለበቱና ከዕለት ወደ ዕለት ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት እንዲሰጡ ለማስቻል መሆኑን አንስተዋል።

የጥናቱ ግኝት የመምህራንን አቅም ለማጎልበት የሚደረገው ጥረት ለማጎልበት እንደሚጠቅም አስረድተዋል።

# በበጋ በጎ ፈቃድ አገልግሎት 700 ሺህ ዜጎች ተጠቃሚ ይደረጋሉ

**ዳግማዊት ግርማ**

<u>አዲስ አበባ</u>፦ በበጋ በጎ ፈቃድ አገልግሎት 700 ሺህ ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን የአዲስ አበባ ህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን አስታወቀ። 100 ሺህ በጎ ፈቃደኛ የሰላም ሠራዊት በአካባቢ ሰላምና ጥበቃ እንዲሳተፉ ማስተባበር እንደታሰበም ተጠቅሷል።

የበጋ በጎ ፈቃድ አገልግሎት መክፈቻና የበጎ ፈቃደኞች የንቅናቄ መድረክ በአዲስ አበባ ሲካሄድ ንግግር ያደረጉት ኮሚሽነር አብርሃም ታደሰ እንዳሉት፤ በዘንድሮው ዓመት የሚከናወነው የበጋ በጎ ፍቃድ አገልግሎት 700 ሺህ ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል።

እንደ አቶ አብርሃም ንግግር፤ የበጋ በጎ ፈቃድ አገልግሎቱ ከሁለት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ለማዳን የሚያስችል ነው። የበጋ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ከህዳር አንድ እስከ ግንቦት 30/2016 ዓ.ም የሚቆይና 13 መርሃ ግብሮችን ያካተተ ስለመሆኑም አቶ አብርሃም ጠቅሰዋል።

በሰላም እሴት ግንባታ ዙሪያም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለመሥራት ስለመወጠኑ የተናገሩት ኮሚሽነሩ፤ 100 ሺህ በጎ ፈቃደኛ የሰላም ሠራዊት በአካባቢ ሰላምና



ኮሚሽነር አብርሃም ታደሰ

ጥበቃ እንዲሳተፉ ማስተባበር እንደታሰበም ነው የጠቀሱት።

በተመሳሳይ በበጎ ፈቃድ የሚሠሩ የጤና ጉዳዮች በእቅዱ ውስጥ ስለመካተታቸው የገለፁት ኮሚሽነሩ፤ ለ33 ሺህ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውና አቅመ ደካሞች ነፃ መሠረታዊ የህክምና ቅድመ ምርመራና ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ ስለመታቀዱም ጠቅሰዋል።

የበጋው አገልግሎት በጎ ፈቃደኞችን በሁሉም መርሃ ግብሮች ላይ በማሳተፍ የከተማዋን ልማትና እድገት ለማፋጠን እንዲሁም የህብረተሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ጊዜያቸውን፣ እውቀታቸውን፣ ገንዘባቸውን እና ጉልበታቸውን እንዲያበረክቱ ስለማስቻሉም ኮሚሽነሩ ገልጸዋል።

2015 ግንቦት ወር ተጀምሮ መስከረም ሰላሳ በተጠናቀቀው የክረምት በጎ ፍቃድ ሶስት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን የህብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን የከተማዋን ነዋሪዎች ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን አስታውሰዋል። በዚህም አምስት ነጥብ ሁለት ሰባት ቢሊዮን ብር የሚደርስ የመንግስት ወጪን ማዳን ተችሏል ብለዋል፡፡

ኮሚሽነር አብርሃም፤ በየጊዜው እየዳበረ የመጣውን የዜጎች በበጎፈቃድ ተግባራት ላይ የመሳተፍ ባህል አጠናክሮ ለማስቀጠል እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ማንኛውም የህብረተሰቡ ክፍል የበጎ ፍቃድ መርሃ ግብር ላይ እና የከተማ ልማት ሥራ ላይ በፈቃደኝነት እንዲሳተፍ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።



# በዞኑ ከ16 ሺህ በላይ የሚሆኑ ዜጎች በወባ በሽታ ተይዘዋል

**ታደሠ ብናልፈው**

<u>አዲስ አበባ</u>፦ በሰሜን ወሎ ዞን ከ16 ሺህ በላይ የሚሆኑ ዜጎች በወባ በሽታ መያዛቸውን የዞኑ ጤና መምሪያ አስታወቀ፡፡ የወባ በሽታ ስርጭትን ለመከላከልና በበሽታው የሚጠቁ ሰዎችን ቁጥር ለመቀነስ ከ408 ሺህ በላይ አጎበር መሰራጨቱ ተነግሯል፡፡

የሰሜን ወሎ ዞን ጤና መምሪያ ኃላፊ ሲስተር ፈለቁ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዞኑ ከ16 ሺህ 271 የሚሆኑ ነዋሪዎች በወባ በሽታ ተይዘዋል፡፡ በበሽታው የሚዙ ሰዎችን ቁጥር ለመቀነስ የአጎበር ስርጭት ሥራና የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡

በሰሜን ወሎ 16 ሺህ 271 ነዋሪዎች በወባ በሽታ መያዛቸውን የተናገሩት ኃላፊዋ፤ በወባ የተያዙት ሰዎች ቁጥር ሁሉንም የዕድሜ ክልል ያካተተ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በበሽታው ተይዘው ከታመሙት ውስጥ ከ13 ሺህ በላይ የሚሆኑት ተገቢውን የህክምና አገልግሎት አግኝተዋል፤ በበሽታው የሞተ ሰው የለም ብለዋል፡፡

በዞኑ በሚገኙ አንዳንድ አካባቢዎች ባለው ወቅታዊ የፀጥታ ችግር ምክንያት ለወባ በሽታ እየተሰጠ ያለውን ህክምና አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ እንዳልተቻለ ገልፀዋል፡፡

የፀጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ሕክምናውን ተደራሽ ማድረግ ቢቻልና የቅድም መከላከል ሥራ ቀደም ብሎ ቢሠራ የታማሚዎችን ቁጥር መቀነስ ይቻል ነበር ሲሉም አብራርተዋል፡፡

ችግሩን ለማቃለል በሽታውን ሊያስታግሱ የሚችሉ መድኃኒቶችን እንደ አማራጭ እየተጠቀምን ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የበሽታውን ስርጭት ለመግታት ማህበረሰቡን ያሳተፈ ለወባ ትንኝ መራቢያ የሆኑ ቦታዎችን የመለየት፤ ኬሚካል የመርጨት፣ ያቆሩ ውሃዎችን የማፋሰስ፤ የአካባቢን ንፅህና የመጠበቅና የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም በወባ በሽታ የሚጠቁ ሰዎችን ቁጥር ለመቀነስና የአጎበር ስርጭት የማድረግ ሥራ የተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ባለፉት አራት ወራት 408 ሺህ 649 አጎበር ተሠራጭቷል ብለዋል፡፡

የተሠራጨውም አጎበር ማህበረሰቡ ለታለመለት ዓላማ አውሎ እንዲገለገልበት ቤት ለቤት የማስተማር ሥራ መሠራቱንም አክለው አስታውቀዋል፡፡

በዚህም 741 ሺህ 687 ዜጎች የአጎበር ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ህብረተሰቡ ማንኛውም የህመም ስሜት ሲሰማው ወደ ጤና ጣቢያ በመሄድ የባለሙያ ርዳታና እገዛ ማግኘት ይጠበቅበታል ያሉት ሲስተር ፈለቁ፤ ማህበረሰቡ ያቆሩ ውሃዎችን የማፋሰስ እና ሌሎች የመከላከል ሥራዎችን መሥራት አለበት ሲሉ አሳስበዋል፡፡

ማህበረሰቡን ከወባ በሽታ ለመከላከል እየተሠራ ለው ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ አመላክተዋል፡፡

# በክልሉ የግብርና ሽግግር ፍኖተ ካርታ ሊተገበር ነው

**ፍሬህይወት አወቀ**

አዲስ አበባ፦ በጋምቤላ ክልል ከተያዘው በጀት ዓመት አንስቶ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግና የአርሶና አርብቶ አደሩን ሕይወት ለመቀየር የሚያስችል የግብርና ሽግግር ፍኖተ ካርታ ተግባራዊ እንደሚደረግ የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

የክልሉ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡጁሉ ሉአል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ በክልሉ የግብርና ሽግግር ፍኖተ ካርታ ጥናት በቅርቡ የፌዴራል መንግሥት፣ የክልሉ ከፍተኛ ባለሥልጣናትና ባለሀብቶች በተገኙበት ይፋ ተደርጓል።

ፍኖተ ካርታው የአርሶና አርብቶ አደሩን ሕይወት ለመቀየር የሚያስችል ሲሆን፤ ከተያዘው በጀት ዓመት ጀምሮ በክልሉ ተግባራዊ ይደረጋል።

የክልሉን የግብርና ሥራ በማዘመን አርሶ አደሩንና ከፊል አርብቶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ ከተዘጋጀው የግብርና ሽግግር ፍኖተ ካርታ በርካታ ውጤቶች ይጠበቃሉ ብለዋል ቢሮ ኃላፊው።

በፍኖተ ካርታው መሠረት በክልሉ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የአርሶና አርብቶ አደሩን ሕይወት መለወጥና የወጪ ንግድ ምርቶችን ለማምረት ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ አስታውቀዋል።

በፍኖተ ካርታው በክልሉ በቀጣይ አምስት ዓመታት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ማሳደግ በሚያስችሉ የግብርና ሥራዎች ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራም አስታውቀዋል።

በፍኖተ ካርታው በዋናነት 10 በሚደርሱ የምርት አይነቶች ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራ ጠቅሰው፤ በቆሎ፣ ሩዝ፣ አኩሪ አተር እና የበጋ መስኖ ስንዴ በክልሉ ትኩረት የሚሰጣቸው የሰብል ምርቶች መካከል መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ከፍራፍሬ ማንጎና ሙዝ፣ ከእንስሳት ምርቶች ደግሞ የወተት ምርት፣ የዳልጋ ከብቶች፣ የዓሳ፣ የፍየል፣



የዶሮና ንብ ርባታ ትኩረት ተሠጥቶ እንደሚሠራባቸው አመላክተዋል።

ይህ ሥራ ከፍተኛ ርብርብ ማድረግን እንደሚጠይቅም ተናግረው፤ ፍኖተ ካርታው በቀጣይም ቀስ በቀስ በሌሎች የምርት አይነቶች ላይ እንደሚተገበር ጠቁመዋል።

አቶ ኡጁሉ እንዳሉት፤ በክልሉ የተለመደው መጠነኛ ምርት አምርቶ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮን መምራት ነው። በፍኖተ ካርታው ይህን ልማድ በማስቀረት ጠንካራ የሥራና የቁጠባ ባህል ለመፍጠር ይሠራል።

አርሶና አርብቶ አደሩ ምርቱን በስፋት እንዲያመርትና ምርቱን ከምግብ ፍጆታ ባለፈ ወደ ገበያ አውጥቶ በመሸጥ ገቢ ማግኘት እንዲችል ለማድረግ ፍኖተ ካርታው ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው ብለዋል።

አርሶ አደሩን ከባለሀብቶች ጋር በመቀናጀት የወጪ ንግድ ምርቶችን በስፋት እንዲያመርት ርብርብ እንደሚደረግ አመልክተው፤ ለዚህም በክልሉ የግብርና ሽግግር ፍኖተ ካርታ ማስጀመሪያ መርሃ ግብር ላይ 766 የሚደርሱ ባለሀብቶች እንዲገኙ መደረጉን ተናግረዋል።

ባለሀብቱ ከአርሶ አደሩ ጋር በሚፈጥረው ትስስር ውጤታማ ሥራ መሥራት ይቻላልም ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሲያመልጠን የማይገባ ወርቃማ ዕድል!

ኢትዮጵያውያን እንደ አንድ ማኅበረሰብ የሚለያዩን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ እና ኢኮኖሚያዊ እሳቤዎች አሉ። እነዚህ እሳቤዎች ልዩነቶችን ማስተናገድ የሚያስችል ማኅበረሰብ ለመገንባት ለጀመርናቸው ጥረቶች ስኬታማነት ትልቅ አቅም ሊሆኑ እንደሚችሉ ይታመናል።

በቀደሙት ዘመናት እነዚህን ልዩነቶች በሰላማዊ መንገድ ቁጭ ብሎ ማስታረቅ የሚያስችል የፖለቲካ ሥርዓት መፍጠር ባለመቻላችን፣ ሀገሪቱ በግጭት አዙሪት ውስጥ ዘመናትን አስቆጥራለች። በዚህም በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶች ያልተገባ ዋጋ ለመክፈል የተገደዱበት ሁኔታ የታሪካችን ሰፊ ትርክት የያዘ ነው።

አሁን ላይ ይህንን ችግር ለዘለቄታው በመፍታት፤ ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ ማስተናገድ የሚያስችል የፖለቲካ ሥርዓት ለመፍጠር በሚያስችል ሀገራዊ መነቃቃት ላይ እንገኛለን። ለዚህም ብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን አቋቁመን፣ ለዓላማው ስኬት እንደ ዜጋ የሚጠበቅብንን ለማበርከት እየተንቀሳቀስን ነው።

በርግጥ ይህ ትውልድ እንደ ትውልድ ሰፊ ያደሩ የቤት ሥራዎች በእጁ እንዳሉ ይታመናል። እነዚህ የቤት ሥራዎች ዛሬ ላይ ሕይወትን ጨምሮ ብዙ ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍል፣ የራሱን እጣ ፈንታ ወስኖ፣ በራሱ መንገድ እንዳይኖር ተግዳሮት እየሆኑበት ነው።

ትውልዱ እየተፈተነባቸው ካሉ ያደሩ ሥራዎች በአሸናፊነት ለመውጣት ከሁሉም በፊት፣ በእጁ ያሉትን የቤት ሥራዎች /ችግሮች/ ምንነት በቅጡ ማጤን፣ በቤት ሥራዎቹ ምንነት ዙሪያ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ይኖርበታል። ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጁነት እና ቁርጠኝነትም መፍጠር ይጠበቅበታል።

ለዚህ ደግሞ ለውይይት /ለመነጋገር/ ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት ብዙም አነጋጋሪ አይደለም። ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ሲንከባለሉ የመጡ ሀገራዊ ችግሮቻችንን በሰለጠነ መንገድ ተነጋግረን ለመፍታት የሚያስችል ትልቅ ዕድል መሆኑን አምኖ መቀበልም ያስፈልጋል።

በተለያዩ ወቅቶች፣ በተለያዩ ኃይሎች የኮሚሽኑ መቋቋም በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ወሳኝ እንደሆነ ሞግተዋል ፤ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው አሰምተዋል። አሁን ላይም መላው ሕዝባችን በኮሚሽኑ ላይ ያለው ተስፋ ቀን ተቀን እየጨመረ፤ ለተልዕኮው ስኬት በቁርጠኝነት እየተንቀሳቀሰ ነው።

በርግጥ ከነበርንበትና አሁንም ካለንበት የግጭት አዙሪት ወጥቶ በሰላም መኖር የሚያስችል ሀገራዊ አውድ ተፈጥሮ ማየት የሁሉም ዜጋ መሻት ብቻ ሳይሆን የዕለት ተዕለት ጸሎት ከመሆኑ አንጻር፤ በሕዝባችን ዘንድ ይህንን ዕድል ለመጠቀም የሚታየው መነሳሳት ብዙም ሊያነጋግር የሚገባ አይደለም።

ከዚህ ቀደም በተፈጠሩ የተዛቡ ትርክቶች ሀገራችን ከአንድም፣ ሁለቴ ሕልውናዋ ከፍተኛ አደጋ ውስጥ ገብቶ ተዓምር በሚመስል መልኩ ተርፋለች። ከእንግዲህ ሦስተኛ ዕድል ላይኖራት ይችላል። ይህንን ዕድል በተገቢው መልኩ መጠቀም ሀገርን እንደ ሀገር ከጥፋት መታደግ የሚያስችል መሆኑንም በአግባቡ መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡

ለአብሮነታችን ከአፍራሽና ከነጠላ ትርክት ወጥተን ሁሉንም ኢትዮጵያውያንን ሊሰበስብ የሚችል ትልቅ ሀገራዊ ትርክትን ለመከተል መነጋገር /መወያየት ይገባል፡፡ ይህን እውን ለማድረግ ሀገራዊ ምክክሩ ከእጁ ሊወጣ የማይገባ ወርቃማ ዕድል ነው። ይህንን ተገንዝቦ መንቀሳቀስም የሁሉም ኢትዮጵያዊ ኃላፊነት ነው፡፡

የኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ሊከበር የሚችለው፣ ከራስና ከቡድን ፍላጎት በላይ ለጋራና ብሔራዊ ጉዳዮች ትኩረት ሲሰጥ ነው፡፡ ለሀገራዊ ምክክሩ ሂደት የማይበጁ ቁርሾዎች ሲበዙ፣ ዘለቄታዊ ሰላምና መረጋጋት ለማምጣት አዳጋች እንደሚሆን መረዳት አያቅትም፡፡ ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያን ከራሳቸው ፍላጎት በታች ለማድረግ የሚሹ ካሉ ከታሪክ መማር እንዳለባቸው ማስታወስም ይጠቅማል፡፡

አንድነትና እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ በሀገራዊ ምክክሩ የመሠረት ድንጋይ ማስቀመጥ የዚህ ትውልድ ትልቁ የቤት ሥራ ነው፡፡ ቁርሾን አስወግዶ በመግባባት ላይ የተመሠረተ የጋራ ትርክት መፍጠርም እንዲሁ፡፡ በሰከነ መንፈስ ከራሳችን ታሪክ በጎ በጎውን መማርም ያስፈልጋል፡፡

ይህንን ተጨባጭ እውነታ ታሳቢ በማድረግ፤ ገዥው ፓርቲን ጨምሮ ሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲዎችና የሀገር ጉዳይ የሚመለከታቸው ወገኖች፣ ይህ የሕዝብ ምክክር በተቀላጠፈ መንገድ ይከናወን ዘንድ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ መሰናክሎች እንዳይኖሩ ማገዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለጭቅጭቅና ለውዝግብ በር ከሚከፍቱ ድርጊቶች መራቅም ይጠበቅባቸዋል።

ለተጀመረው በጎ አካሄድ የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሕዝብ ወኪሎችና የፖለቲካ ልሂቃን የሰላም ሃሳቦችን በማቅረብ ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆን የበኩላቸውን ሊወጡ ይገባል። የምክክር ጉዳይ የተወሰነ ቡድን አጀንዳ ሳይሆን ሀገርን ከጥፋት፤ ሕዝብን ከሁከትና ከሰላም እጦት መታደግ የሚያስችል ሕዝባዊ አጀንዳ ነው !


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አሰባሳቢ ትርክት፤ ሀገርን በጸና መሠረት ላይ ለማነፅ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

በእያንዳንዱ የሀገር ሁነት እና ክስተቶች ውስጥ ሰው አለ፣ ፖለቲካ አለ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እሳቤዎች አሉ። ይህች ዓለም የበርካታ የፖለቲካ ሥሪቶችን ያለፈች፣ እያለፈች ያለችና ወደፊትም የምታልፍ ነች፡፡ በታሪክ ውስጥ አንድ ሀገር የነበሩ ብዙ ሆነው አይተናል፡፡ ብዙ የነበሩ ሀገራት ደግሞ አንድ ላይ ተዋህደው አይተናል፤ ሰምተናል፤ እየሆነም ነው፡፡

ኢትዮጵያም በእነዚህ ውስጥ በአንዱ ወይንም በሌላው አልፋለች፡፡ ኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ያላት ሀገር ብትሆንም የተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓት ሳይኖራት ብዙ ክፍለ ዘመናትን ተሻግራለች፡፡ በአያሌው መንግሥታት ስልጣን የሚያስረክቡት በኃይል ሲሆን፤ ይህም ብዙ ዋጋ አስከፍሏታል፡፡

በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ አካል የነበሩ እንደ ሀገረ ኤርትራ እና ጅቡቲ በታሪክ አጋጣሚ ራሳቸውን ችለው ሀገር ሆነዋል። እነዚህ ሁሉ የሆኑት ግን እንዲሁ በአንዲት ጀንበር አይደለም፡፡ በርካታ ውስጣዊና ውጫዊ ገፊ ምክንያቶች ነበሩ፡፡

በኢትዮጵያ አሁናዊ የፖለቲካ ትርክት ውስጥም ለሚስተዋሉ ችግሮች ብዙ መልክ ያላቸው አስተያየቶች ይሰማሉ፤ ይስተዋላሉም። አንዳንዶች በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ የሚስተዋለው ችግር ምንጩ ሕገ መንግሥቱ ነው የሚል ድምዳሜ አላቸው፡፡

ሕገ መንግሥቱ፤ ዘመናት የመጣንበትን የፖለቲካ ትርክትና ሥርዓት ብሎም ነባራዊ ዓለም ባገናዘበ ሁኔታ፤ በየጊዜው ለሚፈጠሩ የዓለም ፖለቲካ ቀውሶችና ከፋፋይ ባህሪያቶች ወይንም አባባሽ ምክንያቶችን እራሱን መታደግ የሚያስችሉ እንዳልሆነም ያመለክታሉ፡፡

ሕገ-መንግሥቱ ከብሔራዊ መግባባት አኳያ ገፊ ሁኔታዎችን የሚንከባከብና ለብሔራዊ መግባባትን በሰፊው ትኩረት ያልሰጠ ነው ብለው ይኮንኑታል፡፡ ከፌደራል ሕገ መንግሥት በትይዩ የተቀረፁ የክልል ሕገ መንግሥቶችም በዚህ የተዛባ እሳቤና ሀገራዊ ስሜት መሸርሸር ላይ ድርሻ የትዬሌለ ስለመሆኑ የሚናገሩ በርካቶች ናቸው፡፡

የሀገሪቱን ሰላምና መረጋጋት፤ ብሔራዊ አንድነት መጎልበት ካስፈለገ ሕገ መንግሥቱን መሻሻል ያስፈልጋልም ይላሉ፡፡ ከዚህ ተቃራኒ የቆሙ ደግሞ፤ የሀገሪቱ አሁናዊ ፈተናዎች ከሕገ መንግሥት ትርክት የዘለለ ወደኋላ ብዙ ክፍለ ዘመናትን የሚጓዝና የተነባበሩ የቤት ሥራዎች ናቸው የሚል የመከራከሪያ ሃሳብ አላቸው።

ችግሮቹ በጊዜያቸው በወቅቱና በአግባቡ መፍትሔ ሳይበጅላቸው መቆየቱ፤ የችግሮች ሁሉ ችግር ነው፤ ችግሮቹን ለመፍታት ወደኋላ ተመልሰን እውነታውን በአግባቡ መገንዘብ ያስፈልገናል ይላሉ።

በርግጥ ለኢትዮጵያ ፈተና የሆናባትን ችግር ከሥር መሰረቱ ማወቅና መረዳት፤ መፍትሔም ማፈላለግ ተገቢ ነው፡፡ አሁን ላይ በልዩነት መነፅር ውስጥ የምትዋልል ሀገር ለነገው ትውልድ አስቀምጠን ማለፍ ለታሪክ ተወቃሽነት፣ ለህሊና ፀፀት የሚዳርገን ነው።

ነገን ዛሬ እንስራ የሚል እሳቤና ፍልስፍና በዓለም ላይ በናኘበት በዚህ ዘመን እኛ በትናንት ላይ ቆመን መቆዘም ረብ የለውም። ለዚህም ከፋፋይ ትርክቶችን እየዘጋን ወደ አሰባሳቢ ትርክቶች የሚወስዱ መንገዶችና አሰራሮች ብሎም የርዕየተ ዓለም እሳቤዎችም ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

ለዚህ ደግሞ ከሁሉም በላይ ወጣቱ ትውልድ አደባባይ የሞሉ ትርክቶችን ከራሱ ከማህበረሰቡና ከሀገር ተጠቃሚነት አንጻር በሰከነ መንፈስ ሊመረምራቸው ይገባል። ለምን ብሎ የሚያጠይቅ እና ሁኔታዎችን በጥልቀት የሚመረምር መሆን አለበት፡፡

በርካታ ሀገራት ብዙ ፈተናዎችን አልፈው አሁን ላይ ደርሰዋል፡፡ ለዘመናት ለሁለት ተከፍለው ይቆራቆዙ የነበሩ ሀገራት ዛሬ አንድነታቸውን አጠናክረው በዓለም ላይ የሚፈሩ ሆነዋል፡፡ ለዚህም አባት ሀገር ጀርመንን ማንሳት ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡

የጀርመን ድምፅ ሬዲዮ የጀርመን መዋሃድን 30ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ባሳፈረው ጽሑፍ እንዲህ ሲል ያትታል፡፡ ‹‹አራት አሥርት ዓመታት ከዘለቀው የቀዝቃዛው ጦርነት በኋላ ነበር በጎርጎሮሳዊው ጥቅምት 3 ቀን 1990 ምሥራቅና ምዕራብ ጀርመን በይፋ የተዋሃዱት። ከውህደቱ አስቀድሞ በምሥራቅ ጀርመን እየበረታ በሄደው ተቃውሞ ጫና ሰበብ በጎርጎሮሳዊው ኅዳር 9 ቀን 1989 ጀርመንን ለሁለት የከፈለው የበርሊን ግንብ ፈረሰ፣ ድንበሩም ተከፈተ። ግንቡ ከፈረሰ ዓመት ሊሆነው ጥቂት ሲቀር የዛሬ 30 ዓመት የሁለቱ ጀርመኖች ውህደት እውን ሆነ። ከውህደቱ በኋላ ብዙ እድገቶች ተመዘገቡ›› ሲል የአንድነት ኃይልነትን ያወሳል፡፡ ይህ ታሪካዊ ክስተት አሰባሳቢ ትርክት የቱን ያህል ኃይል እንደሚያጎናፅፍ አመላካች ነው፡፡

እኛም እንደ ሀገር መሰረታችንን ለማጽናት ከሁሉም በላይ አንድ በሚያደርጉን ትርክቶች ዙሪያ አብዝተን መሥራት ይኖርብናል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ትርክቶቻችን መሠረት ሊያደርጉባቸው በሚገቡ እውነታዎች ዙሪያ የጋራ መግባባት ላይ ልንደርስ ይገባል።

‹‹በሽታውን ያልተናገረ፤ መድኃኒት አይገኝለትም›› እንዲሉ አበው፤ በውስጣችን የተሰነቀሩ አያሌ የተዛቡ አስተሳሰቦችን ማረም ይገባል፡፡ እንደ ሀገር ብሔራዊ መግባባትን ለማምጣትም ፖለቲከኞች፣ የመገናኛ ብዙሃን አውታሮች፣ ምሁራን፣ ማህበረሰብ አንቂዎች፣ እልፍ ኪሎ ሜትሮችን በመጓዝ መፍትሔዎች ምን መሆን አለባቸው በሚለው ላይ መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ለብሔራዊ መግባባት መሠረት የሚጥሉ እና የነጠሩ ሃሳቦችን በማፍለቅ፣ በመተንተን፣ በማስገንዘብ እና ለሀገራዊ አንድነት የተሻሉ እንዲሁም አብዛኛው ሊያስማሙ ወይንም ሊያቀራርቡ የሚችሉ አማራጮችን በማፍለቅ፤ ሀገራችንን እየተፈታተናት ከሚገኘው አደገኛ ትርክት ወደ አሰባሳቢ ትርክት ልንመጣ ይገባል።

ሀገራዊ ተክለ ቁመና በሚያላብሱ ቅቡል ብሎም ዘመን ተሻጋሪ እሳቤዎች ላይ ተመስርተን የነገይቱን ኢትዮጵያ በማይናወጥ ጠንካራ መሠረት ላይ ማዋቀር ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ጊዜው አላለፈም፤ ብዙ ጊዜ አለን።

እንደ ሀገር ድባቴ ውስጥ ያስገቡን ከዛም አልፈው፤ በመከፋፈል፣ በመነታረክና እርስ በእርስ ወደ መቆራቆዝ የወሰዱንን የተዛቡ ትርክቶችን ማስተካከል አለብን፤ ለዚህ ደግሞ ሰፊ የታሪክ ሀብት፤ ከትናንት የወረስናቸው የአኗኗር ዜይቤዎች አሉን፡፡

የነገው ትውልድ መልካም ልምድና ትምህርት የሚቀስምበት የኢትዮጵያን ሕልውና በላቀ ደረጃ የሚያስቀጥልበት የጋራ ትርክት መፍጠር የዚህ ትውልድ አሁናዊ ሥራ ነው፡፡ ለሀገር አንድነት ፈተና የሆኑ ከፋፋይ እና ከስንዴ ምርት ለመቀላቀል የሚቋምጡ እንክርዳድ የሆኑ አስተሳሰቦች ከታሪክ ገጽ ማስወገድም ዘላቂ መፍትሔ ነው፡፡

# ክልሉ በመዲናዋ የተገነቡ የገበያ ማዕከላት ተሞክሮን በመውሰድ ተግባራዊ ሊያደርግ ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የተገነቡ የገበያ ማዕከላት እና የሸማች ማህበራት በአማራ ክልል የገበያ ተደራሽነትን ለማስፋት ተሞክሮ በመውሰድ ተግባራዊ እንደሚያደርግ የአማራ ክልል የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ከፍተኛ የሥራ አመራሮች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተገነቡ የገበያ ማዕከላት እና የሸማች ማህበራትን ጎብኝተዋል።

የአማራ ክልል የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ኃላፊ ኢብራሂም መሀመድ፤ በአዲስ አበባ ካሉት የገበያ መዕከላትና ሸማች ማህበራት ተሞክሮ በመውሰድ በክልሉ ተመሳሳይ የገበያ ማዕከላትን ለመገንባት ይሠራል ብለዋል።

ከጉብኝቱ ባሻገር የመዲናዋ የገበያ ማዕከላት ጋር የተጠናከረ የምርት ግብይት ትስስር የመፍጠር ዓላማ አለን ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ ለዚህም ከአዲስ አበባ የንግድ ቢሮ ጋር መግባባት ላይ ተደርሷል ብለዋል።

ጉብኝቱ በአማራ ክልል ከተሞች መሰል የገበያ ማዕከላትን ለማስፋት ተሞክሮ የወሰድንበት ነው ብለዋል።

ከመዲናዋ አመራሮች በተደረገው ስምምነት መሠረት የአማራ ክልል አምራቾችና የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች ምርቶቻቸውን በአዲስ አበባ የገበያ ማዕከላት በብዛትና በጥራት የሚያቀርቡ መሆኑንም አያይዘው ገልጸዋል።

በጉብኝቱ የተሳተፉት በአማራ ክልል የደብረ ብርሃን ከተማ ምክትል ከንቲባ ወርቃለማሁ ኮስትሬ በበኩላቸው፤ በጉብኝታቸው በገበያና በምርት አቅርቦት



አቶ ወርቃለማው ኮስተሬ



አቶ ኢብራሂም መሃመድ

ዙሪያ ጥሩ ተሞክሮ ማግኘታቸውን ገልጸዋል።

የገበያ ማዕከላትን መገንባት በሕገ ወጥ ደላሎች የሚደርሰውን የገበያ አሻጥር የሚያስቀርና የገበያ መረጋጋት የሚፈጥር ነው ያሉት ከንቲባው፤ መሰል የገበያ ማዕከላትን በክልሉ ከተሞች ለማስፋት በትብብር እንደሚሠራም ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ መስፍን አሰፋ እንደገለጹትም፤ የከተማ አስተዳደሩ የገበያ ማዕከላትን በማስፋት የዋጋ ንረትን ለመከላከልና በዝቅተኛ ገቢ የሚተዳደሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

የአማራ ክልል አምራቾችና የህብረት ሥራ ዩኒየኖች በእነዚህ የገበያ ማዕከላት ምርቶቻቸውን እንዲያቀርቡ መግባባት ላይ መደረሱንም አክለው ገልጸዋል።

እንደ አቶ መስፍን ገለፃም፤ የከተማ አስተዳደሩ በአጭር ጊዜ ገንብቶ ለአገልግሎት ዝግጁ ያደo

ረገው የለሚ ኩራ ዘመናዊና ሁለ ገብ የግብርና ምርቶች የገበያ ማእከል በከተማዋ በአቅርቦትና ፍላጎት ባለመጣጣም ምክንያት የሚስተዋል የኑሮ ውድነት ጫና ለማቃለል ከፍተኛ አቅም የሚፈጥር ነው።

ከዚህም በተጨማሪ ገበያ ማእከሉ የምርት ብክነትን ለማስወገድ፣ ምርት ጥራትን ለማስጠበቅ፣ የንግድና ግብይት ሰንሰለቱን ለማሳጠር በማስቻል ምርቶች ዋጋ ንረትን በመቆጣጠር ኑሮ ውድነትን በዘላቂነት ለመቅረፍ አጋዥ መሆኑም ተናግረዋል።

# “ቀይ ባሕር...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

መሆናን አንስተውም፤ ቀይ ባህር አካባቢ ግራና ቀኝ የሚገኙት ሀገራት መልካም ጎረቤቶች ሆነን የሁላችንም ዕጣ ፈንታ የተሻለ ማድረግ እንደሚገባ መክረዋል።

ጎረቤት ሀገራት በዚህ የሚስማሙ ከሆነም ውጤቱ የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ መሆኑን ገልጸዋል።

ሁላችንም ተጠቃሚ የምንሆንበትን መንገድ ከመረጥን ቀይ ባህር ትልቅ አቅም ነው ሲሉም አብራርተዋል።

እጅ ለእጅ ተያይዘን እንደ አንድ ማህበረሰብ አብረን እንደግ ካልን ኢትዮጵያ ለሌሎች የምትሰጠው በርካታ ሀብት አላት፣ ከሌሎች የምታገኘውም ብዙ ነገር አለ ብለዋል።

እንደ ፕሮፌሰር አድማሱ ገለፃ፤ ኢትዮጵያ ከጎረቤቶቿም ሆነ ከሌሎች ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ ነው። የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሃሳብ በባህር በር ጉዳይ የጋራ ጥቅም ስላለን እንነጋገርና እንወያይ የሚል መንፈስ ያዘለ ነው።

ሰጥቶ መቀበል የሚለው አስተሳሰብ ገበያ እንፍጠር ማለት መሆንኑ አመልክተው፤ “ገበያ የሚሄድ ሰው ከራሱም እንድ ነገር ይሰጣል፣ የሌለውን ደግሞ ከሌሎች ያገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

ከዚህ አኳያ የባህር በር ጉዳይ በሰጥቶ መቀበል መርህ ምላሽ እንዲያገኝ ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራ መሥራት ይጠይቃል ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ የባህር በር ባለቤትነትም ኢትዮጵያን ተሰሚነትና ገናናነት የሚያመጣ ስለሆነ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን ሃሳብ መደገፍ አለብን ሲሉ ጥሪ አስተላልፈዋል።

# የአየር መንገዱ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ይቀንሳሉ፤ 50 በመቶ የድምፅ ብክለት ያስቀራሉ ተብሏል።

የአየር መንገዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መስፍን ጣሰው ከሁለት ወራት በፊት በቱርክ የኢኮኖሚ መዲና ኢስታምቡል በተካሄደው የዓለም አቪዬሽን ጉባዔ ላይ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2035 ላይ የአውሮፕላኖቹን ቁጥር 271 የማድረስ እቅድ እንዳለው አስረድተዋል። የ 130 አውሮፕላኖችን ግዢ እንደሚፈጽም ማስታወቃቸውም የሚታወስ ነው። ሁለቱ ስምምነቶች አየር መንገዱ በ2035 ለመድረስ ያስቀመጠውን ራዕይ መሠረት ያደረጉ መሆናቸው ተጠቅሷል።

አየር መንገዱ ባሳለፍነው ሳምንት ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችን ጨምሮ የተለያዩ ሀገራት አምባሳደሮች በተገኙበት ከፍተኛ እምርታ ያስመዘገበበትን የካርጎ ደንበኞች ቀንን አክብሯል።

በዕለቱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ጣሰው አየር መንገዱ ከ67 በላይ በሆኑ መዳረሻዎቹ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የካርጎ አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ ተናግረዋል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመራጭ የካርጎ አየር መንገድ መሆን መቻሉንም ገልፀዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ካርጎ አገልግሎት በአፍሪካ ትልቁ የአየር ጭነት አጓጓዥ ነው። 16 አውሮፕላኖችን ለካርጎ አገልግሎት መድቦ አስተማማኝ የካርጎ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። አየር መንገዱ በካርጎ አገልግሎቱ ባለፈው ዓመት 740 ሺህ ቶን ጭነት አጓጉዟል። በተያዘው ዓመትም የካርጎ አገልግሎቱን ወደ አንድ ሚሊዮን ለማሳደግ እየሠራ ነው።

አየር መንገዱ የካርጎ ደንበኞች ቀንን ሲያከብር በዘጠኝ የኤክስፖርት ምድቦች ከፍተኛ አፈፃፀም በማስመዘገብ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ደረጃ ለያዙ 27 ኤክስፖርተሮች እውቅና ሰጥቷል።

ጀጀ ቴክስታይል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በአዲስ አበባ ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚገኝ አምራች ኢንዱስትሪ ነው። የሚያመርታቸውን አልባሳት ሙሉ ለሙሉ ወደ ውጭ ነው የሚልከው። በዋናነትም ምርቶቹን የሚያቀርበው ለአሜሪካ ገበያ ነው።

"ላለፉት ስምንት ዓመታት በኢትዮጵያ አየር መንገድ ካርጎ ተጠቅመናል፤ በአገልግሎታቸው ደስተኛ ነን። በሽልማቱ በሌዘርና ቴክስታል ዘርፍ አንደኛ ደረጃ አግኝተናል" ያሉት ሽልማቱን የተቀበሉት የድርጅቱ ተወካይ ወደፊትም ያገኘነውን ደረጃ ለማስጠበቅ ተግተን እንሠራለን ብለዋል።

አያይዘውም ለሀገር ይህን ያህል አስተዋጽኦ ማድረግ ቀላል ነገር ስላልሆነ እውቅና በማግኘታችን ትልቅ ደስታ ተሰምቶናል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ በካርጎ አገልግሎቱ አመርቂ ውጤት እያስመዘገበ ነው። በሀገራችን በርካታ ኤክስፖርተሮች አሉ። እነዚህ አምራችና ላኪዎች የአየር መንገዱን ካርጎ እንዲጠቀሙ ያነሳሳቸዋል ብዬ አስባለሁ ሲሉ ገልጸዋል።

በቡና ኤክስፖርት ዘርፍ የተሠማራው ትራኮን ትሬዲን ሦስተኛ ደረጃን በመያዝ ተሸላሚ ለመሆን የበቃ ድርጅት ነው። ሽልማቱን የተቀበሉት የድርጅቱ ተወካይ ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማቸው ገልጸው፤ "የልፋታችንን ውጤት ነው ያገኘነው። የበለጠ ተግተን እንድንሠራ ትልቅ ሞራል የሚሰጥ ሽልማት ነው። አየር መንገዱ እንዲህ ያለ የእውቅና መድረክ መፍጠሩ ኤክስፖርትን የሚያበረታታ ነው" ብለዋል።

አክለውም ሽልማቱ ሌሎች ድርጅቶች የዛሬ ተሸላሚዎችን ተመልክተው ይበልጥ ተግተው እንዲሠሩ እንደሚያነሳሳ ተናግረዋል። በውጤቱም የሀገሪቱ የወጪ ቀጥተኛ ንግድ እንዲያድግ በማድረግ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን እንደሚያሳድግ ገልጸው፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድን አመስግነዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአሁኑ ወቅት 147 አውሮፕላኖች ያሉት ሲሆን፣ ከቦይንግ እና ከኤር ባስ የታዘዙት 78 አውሮፕላኖች ሲጨመሩ ቁጥሩ ወደ 225 ከፍ ይላል። አየር መንገዱ እያደረገ ያለው የግዢ ስምምነት የደንበኞቹን ምኞትና ፍላጎት በመጠበቅ ተመራጭነቱን ለማሳደግና ተደራሽነቱን ለማስፋት ከአፍሪካ ቀዳሚ ሆኖ መዝለቅ እንዲችል ያገዘዋል ተብሎ ይጠበቃል።

# የኢትዮጵያ ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት እንደሚደረግ የገለጹት አቶ በኃይሉ፤ በተያዘው በጀት ዓመት ተልባ፣ የጉሎ ፍሬ እና ጤፍ በዘመናዊ ግብይት ሥርዓት ለማገበያየት እቅድ መያዙን ገልጸዋል።

ባለፉት ሦስት ዓመታት የግብርና ምርታማነትን በማሳደግ በምግብ እህል አቅርቦት እራስን ለመቻል ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷል። ይህም በግብርና ምርቶች ላይ የምርት ጭማሪ እንዲኖር ያደርጋል። ከዚህ አንፃር በምርት ገበያው የሚያገበያያቸው ምርቶች በሀገር ውስጥ ገበያ ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድሩ የበኩሉን ሚና ይጫወታል ብለዋል።

ሌላው ከግብርና ምርቶች ውጪ እንደቆዳና ሌጦ፣ ጨው የመሳሰሉ ምርቶች ወደ ግብይት ሥርዓቱ እንዲገቡ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ በኃይሉ፤ የኢንዱስትሪ ምርቶችን ወደ ግብይት ሥርዓቱ ለማስገባት ጥናቶች እየተደረጉ ነው። ይህም የግብይት ሥርዓቱን ለማጠንከር እና በግብይት ሥርዓቱ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመለየት ይረዳል ብለዋል።

እንደ አቶ በኃይሉ ገለፃ፤ ምርት ገበያ የግብይት ሥርዓቱንና አገልግሎቱን በማሻሻል አርሶ አደሩን፣ አቅራቢው፣ የሕብረት ሥራ ማህበራትንና ላኪዎችን በማገልገል ላይ ነው። ሀገሪቱ ከውጭ ምንዛሬ የምታገኘውን ገቢ ለማሳደግ ጥረት እያደረገም ነው።

ከሚደረገው ጥረት ውስጥ የበይነ መረብ ግብይት ማስጀመር፤ ተጨማሪ የግብርና ምርቶችን ወደ ግብይት ሥርዓቱ ማስገባትና ያሉትን የግብይት መጠን መጨመር እንዲሁም የመጋዘን ደረሰኝ የብድር አገልግሎትን ማስፋት ተጠቃሽ ናቸው ብለዋል።

የዘንድሮ በጀት ዓመት ሲጠናቀቅ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ 37 ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸው የተለያዩ ምርቶችን ለማገበያየት እየተሠራ ነው ያሉት አቶ በኃይሉ፤ ምርት ገበያው በ2015 በጀት ዓመት 24 ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸውን 257 ሺህ ሜትሪክ ቶን የተለያዩ ምርቶችን ማገበያየቱን አስታውሰዋል።

አኩሪ አተር እና ቡና ከፍተኛው ግብይት የተፈጸመባቸው ምርቶች እንደሆኑም ጠቅሰዋል።

# ኢትዮጵያን በሰው ሠራሽ አስተውሎት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

በነዚህ ዓመታትም በርካታ ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል።

በዋናነት ኢንስቲትዩቱ ከሚሠራቸው ሥራዎች አንዱ ኢትዮጵያን በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ቴክኖሎጂ ከአፍሪካ ግንባር ቀደም የሚያደርጋትን ተቋም እውን ማድረግ ነው ብለዋል።

ይህን ተቋም እውን ለማድረግም በዓለም ላይ በዘርፉ ተወዳዳሪ የሚያደርገው የዳታ ማስቀመጥ ሥራ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ዳታ ካስቀመጡ በኋላም የመተተንና ሥራ ላይ የማዋል ሂደቱ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

እንደ ኢንጂነር ወርቁ ገለጻ፤ አሁን ላይ ኢንስቲትዩቱ በጤና፣ በግብርና እዲሁም እንደ ሀገር አጠቃላይ የዳታ ትንታኔዎች ላይ እየሠራ የሚገኝ ሲሆን አራት ሀገርኛ ቋንቋዎችን የያዘ መተግበሪያ አልምቶ ወደ ሥራ አስገብቷል።

መተግበሪያው መረጃዎችን ከጽሁፍ ወደ ድምጽ እንዲሁም ከድምጽ ወደ ጽሁፍ መቀየር የሚያስችል እንዲሁም አራቱን ሀገርኛ ቋንቋዎች መተርጎም የሚችል ነው መሆኑን አስረድተዋል።

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የሀገርን፣ የተቋማትንና የግለሰብን አፈጻጸምና ምርታማነት የሚጨምር ቴክኖሎጂ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ አሁን ባለው ቴክኖሎጂን ያልተላበሰ አሠራር በመፍታት ምርታማነት በእጥፍ መጨመር የሚያስችል መሆኑን ነው የገለጹት።

ዳይሬክተሩ፤ ዓለም በዚህ ቴክኖሎጂ ውድድር ውስጥ መሆናን ጠቁመው፤ ኢትዮጵያም በአፍሪካም ሆነ በዓለም ግንባር ቀደም ለመሆን በተለያዩ ዘርፎች ላይ እየሠራች እንደምትገኝ ተናግረዋል።

ቴክኖሎጂውን በተማረ የሰው ኃይል ለመደገፍም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙ አብራርተዋል።

በዚህ ዓመትም በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በዶክትሬት (PHD) ደረጃ ተማሪዎችን ለማስተማር ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን የተማሪዎች ምልመላ እየተደረገ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

በቀጣይም በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንደ አንድ የትምህርት አይነት ሆኖ እንዲሰጥ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ነው ሲሉም አክለዋል።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የጋምቤላ ክልልን የግብርና ምርትና ምርታማነት የሚያሳድገው ፍኖተ ካርታ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የጋምቤላ ክልል ለግብርና ልማት ሥራ ሊውል የሚችል ለም አፈር፣ በቂ ዝናብ፣ የከርሰ ምድር እና ገጸ ምድር ውሃ ሀብት ባለቤት ነው፡፡ በክልሉ ያለውን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት በመጠቀም ግብርናን በማስፋት ውጤታማ ሥራ መሥራት እንደሚቻል ይታመናል፤ በዚህም ምንም እንኳ በሚፈለገው ልክ ጥቅም ላይ ባይውልም ሰፊ የመስኖ ልማት ለማካሄድ የአልዌሮ ግድብ መገንባቱ ይታወቃል፡፡ በኢህዴግ ዘመን ደግሞ ምንም እንኳ ልማቱን ባያካሂዱም፣ በርካታ ባለሀብቶች ለግብርና ኢንቨስትመንት ወደ ክልሉ የገቡበት ሁኔታም እንደነበር ይታወሳል፡፡

በአሁኑ ወቅት ደግሞ የክልሉ መንግሥት ለግብርናው ሥራ ሊውል የሚችለውን እምቅ ሀብት የበለጠ ጥቅም ላይ ለማዋል እየሰራ ይገኛል። በክልሉ የግብርና ሥራ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲሁም የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የግብርና ሽግግር ፍኖተ ካርታ ጥናት በቅርቡ ይፋ ተደርጓል፡፡

የግብርና ሽግግር ፍኖተ ካርታ ጥናቱ የድርጊት መርሃ ግብሩን የጀመረ ሲሆን፤ ከተያዘው 2016 በጀት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ ይደረጋል፤ በፍኖተ ካርታው መሠረት በክልሉ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የአርሶና አርብቶ አደሩን ሕይወት መለወጥና የኤክስፖርት ምርቶችን ለማምረት ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሰራ የክልሉ የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡጁሉ ሉአል አስታውቀዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ በክልሉ ይፋ የተደረገው የግብርና ፍኖተ ካርታ የሚመለከታቸው የፌዴራልና የዞን አመራሮች፣ ባለሀብቶችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተገኙበት የትውውቅና የተግበራ መርሃ ግብሩ አንድ ብሎ ጀምሯል፡፡ የክልሉን የግብርና ሥራ በማዘመን አርሶ አደሩንና ከፊል አርብቶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ በተዘጋጀው ከዚህ የግብርና ሽግግር ፍኖተ ካርታ በርካታ ውጤቶች ይጠበቃሉ፡፡

በፍኖተ ካርታው በክልሉ በቀጣይ አምስት ዓመታት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ማሳደግ በሚችሉ የምርት ዓይነቶች ላይ ትኩረት አድርጎ እንደሚሰራ የጠቆሙት አቶ ኡጁሉ፤ በተመረጡ የምርት ዓይነቶች የሚጀመረው ሥራም ከፍተኛ ርብርብ የሚጠይቅና ውጤት የሚጠበቅበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በቀጣይም ቀስ በቀስ ወደ ሌሎች ምርቶች በመሄድ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥና ኤክስፖርት ላይ ትኩረት አድርጎ በመሥራት የውጭ ምንዛሪ በማምጣት የሀገሪቷን ኢኮኖሚ ከፍ ማድረግ ይቻላል ብለዋል፡፡

ክልሉ ለግብርና ሥራ ምቹ እንደመሆኑ በፍኖተ ካርታው በዋናነት አስር የሚደርሱ ምርቶች ላይ ትኩረት ተደርጎ የሚሠራ ይሆናል፡፡ በቆሎ፣ ሩዝ፣ አኩሪ አተር እና በሀገር ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት በበጋ መስኖ እየለማ ያለው ስንዴ በፍኖተ ካርታ ከሚለሙ የሰብል ምርቶች መካከል ይገኙበታል፡፡ ከፍራፍሬ ማንጎና ሙዝ፣ ከእንስሳት ምርቶች ደግሞ የወተት ምርት፣ የዳልጋ ከብቶች፣ የዓሳ፣ የፍየል፣ የዶሮና ንብ እርባታ ትኩረት ይደረግባቸዋል፡፡

ከዚህ ቀደም አጠቃላይ በጋምቤላ ክልል የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀምን አስመልክቶ በተደረገ ጥናት በተለይም ለእርሻ ኢንቨስትመንት ምቹ የሆኑ አነስተኛና ሰፋፊ የእርሻ ቦታዎች ተለይተው መቀመጣቸውን አቶ ኡጁሉ ገልጸዋል፡፡ አያይዘውም ለቱሪዝም መስህብ የሚሆኑ ፓርኮችም መለየታቸውንም ጠቅሰዋል፡፡

ለመስኖ ሥራ የሚውሉ አራት ትላልቅ ወንዞች በክልሉ እንደሚገኙ ጠቅሰው፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ የደን ውጤቶችም በስፋት ይገኛሉ ብለዋል። ክልሉ በማዕድን ሀብት እምቅ አቅም እንዳለው ተናግረው፣ በተለይም ወርቅ በአካባቢው በስፋት እንደሚገኝ ነው የጠቆሙት፡፡

‹‹ለቀጣይ አምስት ዓመት ተግባራዊ የሚሆነው የግብርና ሽግግር ፍኖተ ካርታ ወደ ሥራ የሚገባው በክልሉ የሚገኙትን እነዚህን እምቅ ሀብቶች መሠረት በማድረግ ነው›› ያሉት አቶ ኡጁሉ፤ ይህ የግብርና ሽግግር ፍኖተ ካርታ በክልሉ በመደበኛው የግብርና ሥራ ከሚሰራው ሥራ ጎን ለጎን የሚሰራ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ በአስሩ የምርት ዓይነቶች ላይ ትኩረት በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንደሚሰራ ጠቅሰው፣ ኤክስፖርትን ዓላማ በማድረግ የሚሠራ መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

ፍኖተ ካርታው መሠረት የአርሶ አደሩን ሕይወት በመለወጥ ረገድም ትልቅ ድርሻ እንዳለው የጠቀሱት አቶ ኡጁሉ፤ በተለይም በክልሉ ያለውን ጎጂ ልማዳዊ አመለካከቶችን በማስወገድ አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ይላሉ፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ በክልሉ የተለመደው መጠነኛ ምርት አምርቶ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮን መምራት ነው፡፡ በፍኖተ ካርታው ይህን ልማድ በማስቀረት ጠንካራ የሥራ ባህል እና የቁጠባ ባህልን ይፈጥራል። በዚህም አርሶ አደሩ ምርቱን በስፋት እንዲያመርትና ምርቱን ከምግብ ፍጆታ ባለፈ ወደ ገበያ አውጥቶ በመሸጥ ገቢ ማግኘት የሚያስችል ይሆናል፡፡

በክልሉ አርሶ አደር ያልተለመደውን የሥራና የቁጠባ ባህል በማለማመድ በተለይም በተመረጡ አስር የምርት ዓይነቶች ላይ የሚደረገው ርብርብ አርሶ አደሩን ወደ ባለሀብትነት ማምጣት የሚያስችል እንደሆነ አቶ ኡጁሉ ጠቁመዋል፡፡ ከገቢው ቆጥቦ የግብርና ሥራውን በማስፋት ቀስ በቀስ ወደ ባለሀብትነት እንዲሸጋገር የማድረግ ልምድ እንዲያዳብር ይጠቅማል፡፡

እያንዳንዱ አርሶ አደር ምርቱ ምን ያህል እንደሆነ በማጥናት በቀጣይ ከራሱ የምግብ ፍጆታ ባለፈ ወደ ገበያ ማውጣት የሚያስችለውን ምርት ማምረት እንዲችል በዕቅድ ተይዞ የሚሰራ መሆኑ በፍኖተ ካርታው ላይ የተመላከተ ስለመሆኑም አብራርተዋል።

የቢሮ ኃላፊው እንዳሉት፤ ይህም የአርሶ አደሩን ሕይወት በመለወጥ ረገድ ትልቅ ድርሻ ያለው ሲሆን፤ ከዚህም ባለፈ አርሶ አደሩ ከባለሃብቶች ጋር በመቀናጀት የኤክስፖርት ምርቶችን በስፋት እንዲያመርቱ ርብርብ ይደረጋል፡፡ ለዚህም በክልሉ የግብርና ሽግግር ፍኖተ ካርታ ማስጀመሪያ መርሃ ግብር ላይ 766 የሚደርሱ ባለሃብቶች እንዲገኙ ተደርጓል፡፡ እነዚህ ባለሃብቶች ከአርሶ አደሩ ጋር ትስስር በመፍጠር የሚሠሩ ሲሆን፤ ይህም ለክልሉ አርሶ አደር ሕይወት መሻሻልና ለግብርና ሥራው ውጤታማነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ባለሀብቱ ከአርሶ አደሩ ጋር በሚፈጥረው ትስስር ውጤታማ ሥራ መሥራት ይቻላል ያሉት አቶ ኡጁሉ፤ አንድ ባለሀብት በሚሰራበት አካባቢ ላይ አንድ ቀበሌ አርሶ አደሮችን መለወጥ አለበት ብለዋል፡፡ ይህ እንደ አቅጣጫ የተቀመጠ መሆኑን ጠቅሰው፣ በተለይም አቅም ያላቸው ባለሀብቶች በአቅራቢያቸው የሚገኙ ቀበሌዎችን በማገዝ የአርሶ አደሩን ሕይወት ከግብርና ፍኖተ ካርታው ጋር በማስተሳሰር ውጤታማ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው አመላክተዋል፡፡

እንደ አቶ ኡጁሉ ማብራሪያ፤ በክልሉ አርሶ አደሩ ባለው አነስተኛ የእርሻ መሬት በስፋት የሚያመርተው በቆሎና ማሽላ ነው፤ አርሶ አደሩ ለእነዚህ ምርቶች ከፍተኛ ፍላጎት ያለው ቢሆንም፣ ግሪሳ ወፍ የሚያስቸግርበት ሁኔታ በመኖሩ በተለይም ማሽላ የማምረት ፍላጎቱ ቀንሷል፡፡

በአሁኑ ወቅት በክልሉ የሚገኙ ባለሀብቶች ሰፋፊ በሆኑ የእርሻ መሬት ላይ አኩሪ አተር፣ ሩዝ፣ ማሾና የመሳሰሉት እያመረቱ ናቸው፡፡ አብዛኛው የክልሉ ሕዝብ ከፊል አርብቶ አደር እንደመሆኑ ለእንስሳት እርባታም ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ማሳደግ ይቻላል፡፡ በክልሉ ከፍተኛ የዓሳ ሀብት ይገኛል፡፡ 19 የሚደርሱ የዓሳ ዝርያዎችም አሉ፤ ዓሳ በክረምት ወቅት በብዛት ይገኛል፡፡

በአሁኑ ወቅት የመኸር የእርሻ ሥራ ማለፉን ጠቅሰው፣ በክልሉ የወንዞች ሙላት እየቀነሰ ሲሄድ የሚሰራው የግብርና ሥራ ውሃ ሸሽ ሥራ እንደሆነ አቶ ኡጁሉ ተናግረዋል፡፡ በውሃ ሸሽ የግብርና ሥራ 37 ሄክታር መሬት በዘር ለመሸፈን ታቅዶ እየተሰራ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

> **ክልሉ ለግብርና ሥራ ምቹ እንደመሆኑ በፍኖተ ካርታው በዋናነት አስር በሚደርሱ የግብርና ምርቶች ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሰራል፡፡ በቆሎ፣ ሩዝ፣ አኩሪ አተር እና በሀገር ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት በበጋ መስኖ እየለማ ያለው ስንዴ በፍኖተ ካርታ ከሚለሙ የሰብል ዓይነቶች መካከል ይገኙበታል**

በአሁኑ ወቅት በአየር መዛባት ምክንያት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እየጣለ መሆኑን ጠቅሰው፣ አርሶ አደሩ በውሃ ሸሽ እርሻ በዘር የሸፈነው መሬት እየተበላሸ መሆኑን አመላክተዋል፡፡ ውሃ ሸሽ ግብርና ወንዞች ሞልተው ሲቀንሱ አርሶ አደሩ እርጥበቱን ተከትሎ የሚዘራበት የእርሻ ሥራ እንደሆነ አቶ ኡጁሉ ገልጸው፤ በዚህ መልኩ የተዘራው ዘር ከተሰበሰበ በኋላም የመስኖ እርሻ እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡

በክልሉ አንዳንድ አካባቢዎች ከፍተኛ ዝናብ እየጣለ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ኡጁሉ፤ ዝናቡ የደረሱ ሰብሎችን ለመሰብሰብ አስቸጋሪ ሁኔታ መፍጠሩን ጠቁመዋል፡፡ በበጋ መስኖ ለማልማት የታቀደውን ሥራም እያስተጓጎለ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ በተያዘው በጀት ዓመት ብቻ በመስኖ የእርሻ ሥራ 6ሺ500 ሄክታር መሬት ለመሸፈን ታቅዶ እየተሰራ ሲሆን፤ በዚህም ስንዴን ጨምሮ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ሩዝና የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የሥራሥር ልማት ለማካሄድ ታቅዶ የቅድመ ዝግጅት ሥራ እየተሰራ ነው፡፡ ዝናቡ ቆም ሲል በየካቲትና መጋቢት አካባቢ ወደ ሥራ የሚገባ ይሆናል፡፡

ዝናብ በሌለባቸው አካባቢዎች የበጋ መስኖ ሥራው መጀመሩን ጠቅሰው፣ ከበጋ መስኖ ልማት 827 ሺ ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅም አስታውቀዋል፡፡ በውሃ ሸሽ ከተመረተው ምርትም እንዲሁ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ አቶ ኡጁሉ ጠቁመዋል፡፡

የግብርና ቴክኖሎጂ ለምርትና ምርታማነት እጅግ አስፈላጊ እንደሆኑ የጠቀሱት አቶ ኡጁሉ፤ መንግሥት ለክልሉ ትራክተሮችን ማቅረቡንም አስታውቀዋል። በቅርቡም ለመስኖ ሥራ አገልግሎት የሚውሉ 16 የሚደርሱ ትራክተሮችን ለማቅረብ መንግሥት ቃል መግባቱን ገልጸዋል፡፡ ክልሉ የአቅም ውስንነት እንዳለበት አመልክተው፣ አሁን ያለው የሜካናይዜሽን አቅርቦት በቂ አለመሆኑን ተናግረዋል፡፡ የፌዴራልም ሆነ የክልሉ መንግሥት የሚያደርጉትን ይህን መሰሉን ድጋፍና ክትትል አጠናክረው እንዲቀጥሉም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

አቶ ኡጁሉ እንደገለጹት፤ በክልሉ በድህረ ምርት ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች ላይ ክፍተቶች አሉ። አርሶ አደሩ የደከመበትን አዝመራ መሰብሰብ እንዳይችል ችግሮች እየገጠሙት ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ምርቱ ሲባክንና አርሶ አደሩም ለፍቶ መና ሲቀር ይስተዋላል፡፡

ለአብነትም በአካባቢው አትንኩኝ የሚባል አረም ስለመኖሩ ገልጸው፤ አረሙ አርሶ አደሩ ምርቱን ማሳ ውስጥ ገብቶ ለመሰብሰብ አያስችለውም ብለዋል። በዚህ ምክንያት አብዛኛው ምርት ማሳው ላይ በስብሶ እንደሚቀርም ጠቁመዋል፡፡ ስለዚህ የበቆሎ፣ የሩዝና የማሽላ መፈልፈያ በአጠቃላይ የድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎች አስፈላጊና የግድ እንደሆኑ አስታውቀዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ወደ ሥራ የገባው የጋምቤላ ክልል የግብርና ሽግግር ፍኖተ ካርታ በጥናቱ መሠረት ተግባራዊ ሆኖ የተፈለገው ውጤት እንዲመዘገብ አመራሩን ጨምሮ እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል፣ ባለሙያዎችና ማህበረሰቡ በቁርጠኝነት ሊሰሩ ይገባል ያሉት አቶ ኡጁሉ፤ በተለይም አመራሩ የግብርና ኤክስቴንሽኖችንን በማጠናከር የክልሉ ሕዝብ ወደ ሥራ እንዲገባ በመቀስቀስ ርብርብ ማድረግ እንደሚገባው አሳስበዋል፡፡ የልማት ቡድን ባለሙያዎች ለአርሶ አደሩ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብ እንዲያደርጉም ጠይቀዋል፡፡

በጋምቤላ ክልል ግብርናን ለማዘመን በተዘጋጀው ፍኖተ ካርታ ማስጀመሪያ መርሃ-ግብር ላይ የተገኙት የግብርና ሚኒስትር ዶክተር ግርማ አመንቴ እንዳሉት፤ የግብርና ሽግግር ፍኖተ ካርታ ጥናቱን ወደ ተግባር የመቀየርና የአርሶና የከፊል አርብቶ አደሩን ሕይወት በመለወጥ ሥራ ላይ በትኩረት ይሰራል፡፡

በክልሉ ለግብርና ልማት ሊውል የሚችለውን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ወደ ልማት በመለወጥ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በትኩረት እንደሚሰራ ሚኒስትሩ አስታውቀዋል፡፡ ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ ክልሉ ለግብርና ልማት አመቺ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ክምችት ያለው ቢሆንም፤ ሕዝቡ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የግብርና ሥራ የሚተዳደር ሆኖ ቆይቷል፡፡ አካባቢው የምግብ ዋስትናውን ማረጋገጥ አልቻለም። በመሆኑም የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን ክልሉ ያለውን እምቅ ሀብት ተጠቅሞ ለሀገር ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት የግብርና ሚኒስቴር አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ አረጋግጠዋል።


የክልሉ መንግሥትም ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን እየሠራ ስለመሆኑ የጠቀሱት ሚኒስቴሩ፤ በግብርናው ዘርፍ በዘመናዊ ቴክኖሎጂና አዳዲስ አሰራሮች ታግዞ እምርታዊ ለውጥ እንዲመጣ ለሚደረገው ጥረት ባለድርሻ አካላት የሚያደርጉት ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥልም ጠይቀዋል። የፍኖተ ካርታው አካል የሆነው የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ስኬታማ እንዲሆን በሚደረገው ርብርብም እንዲሁ አመራሩ፣ ሕዝቡና የዘርፉ ተዋንያኖች በሙሉ የሚጠበቅባቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ከወዲሁ የተጀመረው የድብልቅ ፈተና ዝግጅት

ግርማ መንግሥቴ



ፈተና ዓይነቱ ብዙ እንደሆነ ሁሉ የአፈታተን ሁኔታውም ዘመኑን ተከትሎ እየበዛና እየተሻሻለ መጥቷል። ድሮ የነበረው የአፈታተን ሥርዓት አንድ ወጥ ነበር፡፡ ዛሬ ግን ለቴክኖሎጂ እድገት ምስጋና ይግባውና የፈተና አማራጮች በዝተዋል። ዛሬ፣ የትም ሆኖ መማር እንደሚቻለው ሁሉ፣ የትም ሆኖ ፈተና መፈተን ይቻላል። የትም ሆኖ ተፈታኝ፣ የትም ሆኖ ፈታኝ መሆን ይቻላል። ከፈተና ጋር በተያያዘ ታዲያ የትምህርት ሚኒስቴር ሰሞኑን አንድ መግለጫ አውጥቷል።

ትምህርት ሚኒስቴር ያወጣው መግለጫ የዘንድሮውን የ2016 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የሚመለከት ሲሆን ፈተናው በግንቦት ወር የሚሰጥ መሆኑና የፈተናው አሰጣጥም ድብልቅ (ሀይብሪድ) እንደሆነ ገልጿል። የፈተናው ዝግጅት ከአሁኑ መጀመሩን የሚያመለክተው መግለጫው ድብልቅ ፈተና ማለትም ግማሹ ኦንላይን (የኢንተርኔት ችግር የሌለባቸው አካባቢዎች)፤ የኢንተርኔት ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ደግሞ ከዚህ ቀደም ሲሰጥ በነበረበት አካሄድ በወረቀት የሚሰጥ መሆኑን አስታውቋል።

ይህ የፈተና አሰጣጥ አካሄድ በዩኒቨርሲቲዎች ላይ፣ በመንግሥት በጀት፣ በትምህርት ቢሮዎች ላይ ጫናን እንደሚቀንስ የተነገረ ሲሆን፤ (የአፈታተን ሥርዓቱን በማዘመን) ምንም እንኳን ትምህርት ሚኒስቴር የመግዛት አቅም ባይኖረውም ለፈተናው የሚሆኑ ታብሌቶችን ከመንግሥት ተቋማት ጋር በመነጋገር በፈተናው ወቅት በመዋስ ፈተናው በድብልቅ እንደሚሰጥ መግለጫው አመልክቷል።

እንደ መግለጫ ከሆነ፣ የ2016 ዓ.ም ፈተና ድብልቅ በሆነ መንገድ እንዲሰጥ ከወዲሁ ዝግጅቶቹ እየተደረጉ ሲሆን የሶፍትዌር ሥራው ከወዲሁ ተጠናቋል። ምዝገባውንም በኦንላይን ሲሆን፣ ተፈታኞች በአካል ተገኝተው ፎቶ እንዲነሱ ይደረጋል፡፡ በዚህ ረገድ ቁጥጥሩ ጠበቅ እያለ ይሄዳል።

የተሻሉ የፈተና አዘጋጆች፣ ፈተናዎች እንዳይሰረቁ የሳይበር ጥበቃ፣ የደህንነት ካሜራዎች፣ የተቋማት ትብብር (ኢንሳ፣ ፈተናዎች አገልግሎት)፣ ጥንቃቄ የተሞላበት የፈተና ሕትመት ዝግጅት ከዚህ ቀደሙ በተሻለ መልኩ ጠንካራ ሥራ በጋራ እንደሚሰራ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በመግለጫው ተናግሯል፡፡

የዘንድሮ የ12ኛ ክፍል ተፈታኝ ተማሪዎች ከወዲሁ እራሳቸውን ለመመዘኛ ፈተናው ብቁ እና ዝግጁ እያደረጉ መሄድ ያለባቸው ሲሆን፤ መምህራን፣ ወላጆች፣ መላው የትምህርት ማህበረሰብ ተማሪዎችን እያገዙ ለፈተናው እንዲዘጋጁ ማድረግ አለባቸው ሲልም ነው ሚኒስቴሩ በመግለጫው ያሳሰበው።

በመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ገብተው ባለፉት ሁለት ብሔራዊ ፈተናዎች ማለትም በ2014 እና 2015 ዓ.ም ከተፈተኑት አጠቃላይ ተማሪዎች 50 በመቶ እና ከዛ በላይ አምጥተው ያለፉት እጅግ ጥቂት መሆናቸው ከመገለፁም በላይ፤ በ2014 ፈተና 896 ሺህ 520 ተማሪዎች ተፈትነው ያለፉት 30 ሺህ 034 ወይም 3 ነጥብ 3 በመቶ ብቻ ሲሆኑ፤ በ2015 ዓ.ም ፈተና 845 ሺህ 099 ተማሪዎች ተፈትነው ማለፍ የቻሉት 27 ሺህ 267 ወይም 3 ነጥብ 2 በመቶ ብቻ መሆናቸውም በመግለጫው ተመልክቷል።

በተለይ ፈተናው በየአካባቢው ካሉ ትምህርት ቤቶች ግቢ ውስጥ ወጥቶ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ መሰጠት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ የተመዘገበው ውጤት ብዙሃኑን ያስደነገጠ፤ እንዲሁም፣ የትምህርት ሥርዓቱ ያለበትን አሳሳቢ የሚባል ደረጃ ያመላከተ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ በሂደት ይህ ሁሉ ችግር እየተቀረፈ፤ የተማሪዎች የመማር አቅም እየጎለበተ፤ በመሄድ የተሻለ ውጤት ላይ እንደሚደረስ ይጠበቃል። ይህ ይሆን ዘንድ ታዲያ ተፈታኝ ተማሪዎችን ከወዲሁ በማንቃት ለተሻለ ውጤት እንዲዘጋጁ ማድረግና የተመዘገበው "አስደንጋጭ" ውጤት እንዲለወጥ ማበረታታት ተገቢ መሆኑ ይታመናል፡፡

በታብሌት (የእጅ ስልኮች) ፈተና መፈተን ከተለመደው የወረቀት ፈተና ተጨማሪ እውቀት ይፈልጋል፤ የተለየ ክህሎት ይጠይቃል። በተጨማሪም፣ ጉዳዩ የሶፍትዌር (ወይም፣ አፕሊኬሽን) ነውና የሚሆነው የሶፍትዌር ወይም አፕሊኬሽን አጠቃቀምን ብልሃትንም ይጠይቃል። ይሁን እንጂ፣ ትምህርት ሚኒስቴር "ዝግጅቱን ከወዲሁ ጀምሬያለሁ" ሲል እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ክህሎቶችን በተፈታኝ ተማሪዎች ዘንድ ማስረፅንም ያካትታል ተብሎ ይታሰባልና ጉዳዩ ብዙም የሚያስጨንቅ አይሆንም።

በየትምህርት ቤቶችም በተመሳሳይ መንገድ ተፈታኝ ተማሪዎቻቸውን የማብቃት ሥራዎች ይሰራሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ተፈታኝ ተማሪዎችም ለፈተናው ብዙም በማይጠቅሙ ማህበራዊ ድረገፆች ላይ ጊዜያቸውን ከማጥፋት ተቆጥበው ሙሉ ትኩረታቸውን ጥናትና ዝግጅታቸው ላይ ያደርጋሉ ተብሎ ተስፋ ተጥሏል።

ወደሃይብሪድ/ድብልቅ/ ፈተናው ሲመጣ ደግሞ በተለይ ዓለማችን አሁን ያለችበትን አጠቃላይ ሁኔታ ለተመለከተ ቴክኖሎጂ ምን ያህል እንደተቆጣጠረን በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ዛሬ፣ ከተራ ማህበራዊ ግንኙነት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ መንግሥታዊ ተግባራት ድረስ ያለ ቴክኖሎጂ የሚከናወን ነገር የለም። እዚህ ሆኖ አውሮፓ ፈተና መፈተን፣ እዚህ ሆኖ አሜሪካን ሀገር ከሚገኝ ተቋም ጋር ቃለ መጠይቅ ማድረግ ምንም አዲስ ነገር የለውም። በመሆኑም፣ ፈተናን በታብሌት መፈተን ችግሮችን ያቀልላቸዋል እንጂ የሚፈጥረው መሰናክል የለም። ምናልባት እኛን የሚያስወቅሰን ነገር ቢኖር ከቴክኖሎጂው መዘግየታችን ነው።

ሌላው፣ የፈተናው ጉዳይ ሲሆን፣ በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው በነባሩ አሰራር መሠረት በወረቀትና በታብሌት በሚፈተኑት መካከል ከፈተናው አኳያ ምንም ዓይነት የይዘትም ሆነ የቅርፅ ልዩነት አይኖርም፤ ልዩነት አለ ከተባለ ያው የተገለፀው አፈታተኑ ድብልቅ (ሀይብሪድ) መሆኑ ብቻ ነውና በዚህ በኩል ማንንም የሚያሳስብ ምንም ነገር የለም።

ከፈረሱ አፍ እንዲሉ፣ የትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች እንደተናገሩት የመፈተኛ ታብሌቶቹ በተቋሙ አቅም የሚሟሉ ሳይሆኑ የባለ ድርሻ አካላትን፣ የባለ ሀብቶችን ወዘተ ትብብርና እገዛ የሚጠይቁ ናቸው። ከዚህ አኳያ እነዚህ አካላት ፈተናው በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳና በአግባቡ እንዲካሄድ የበኩላቸውን ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል። ትምህርት ሚኒስቴርም (በባለፉት ፈተናዎች እንደታየው) የማስተባበር ችግር ይኖርበታል ተብሎ ስለማይታሰብ የድብልቅ ፈተና ፕሮግራሙ በሚጠበቀው መልኩ ይጠናቀቃል ተብሎ ይታሰባል።

ሌላው የመፈተኛ ጣቢያዎችና ፈታኞች ጉዳይ ሲሆን፣ ሁሉም ቴክኖሎጂውን ማእከል ባደረገና ቴክኖሎጂው የደረሰበትን እድገት ታሳቢ ያደረገ እንደሚሆን ከወዲሁ መገመት አያዳግትም። ፈታኞችም ቢሆኑ ከተፈታኞቹ ያልተናነሰ የቴክኖሎጂ እውቀት እንደሚያስፈልጋቸው ጥርጥር የለም። ያ ካልሆነ ክፍተት መፈጠሩ የሚቀር አይሆንምና ከወዲሁ መፍትሔን ይሻል።

ከላይ፣ "ድብልቅ ፈተና ማለት ግማሹ ኦንላይን (የኢንተርኔት ችግር የሌለባቸው አካባቢዎች)፤ የኢንተርኔት ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ደግሞ ከዚህ ቀደም ሲሰጥ በነበረበት አካሄድ በወረቀት" ይሆናል ተብሏል። በዚህ መሠረት እነማን በነባሩ፣ እነማን ደግሞ በኦንላይን ፈተናውን እንደሚወስዱ ይታወቃል ማለት ነው። ቢያንስ በግርድፉም ቢሆን አካባቢዎቹን መለየት ይቻላል ማለት ነው። እዚህ ጋር ግን አንድ ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ ያለ ሲሆን እሱም ". . . ችግር ባለባቸው" የሚለው ችግር ሳይሆን "ኢንተርኔት ባልተዳረሰባቸው" በሚለው ቢብራራ የተሻለ ይሆናል። ምክንያቱ ደግሞ "ችግር" የሚለው እዚህ፣ አዲስ አበባም ኢንተርኔት ሁሌም ችግር ነውና።

> «በታብሌት (የእጅ ስልኮች) ፈተና መፈተን ከተለመደው የወረቀት ፈተና ተጨማሪ እውቀት ይፈልጋል፤ የተለየ ክህሎት ይጠይቃል። በተጨማሪም፣ ጉዳዩ የሶፍትዌር (ወይም፣ አፕሊኬሽን) ነውና የሚሆነው የሶፍትዌር ወይም አፕሊኬሽን አጠቃቀምን ብልሃትንም ይጠይቃል። ይሁን እንጂ፣ ትምህርት ሚኒስቴር «ዝግጅቴን ከወዲሁ ጀምሬያለሁ»ሲል እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ክህሎቶችን በተፈታኝ ተማሪዎች ዘንድ ማስረፅንም ያካትታል ተብሎ ይታሰባልና ጉዳዩ ብዙም የሚያስጨንቅ አይሆንም»

ቀደም ሲል "አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ" በሚለው መሠረት ሲሰራባቸው የቆዩትን አሰራሮች በስር ነቀል ደረጃ እየለወጠ በመሄድ ላይ መሆኑን የሚናገረው ትምህርት ሚኒስቴር፣ ይህ የድብልቅ አፈታተን ስርአትም የዚያው አካል መሆኑን እየተናገረ ይገኛል። ባፍጢሙ ተደፍቶ የነበረውን የትምህርት ጥራት በሁለት እግሩ ለማቆም እየወሰዳቸው ካሉ ርምጃዎችም አንዱ ይኸው መሆኑን በማስረዳት ላይ ነው። በመሆኑም፣ ልክ ለትምህርት ተደራሽነት ብቻ ሲሰጥ ከነበረው ትኩረት እኩል ለጥራቱም መሰጠት ጀምሯል ማለት ይቻላልና ዘንድሮ ከአምናው የተሻለ የተፈታኞች ውጤት እንደሚጠበቅ ይገመታል፡፡

ሌላው ይህ የድብልቅ ፈተና ፕሮግራም ይዞት ይመጣል ተብሎ የሚጠበቅ አቢይ ጉዳይ ቢኖር ተማሪዎች በራሳቸው የመተማመንና ፈተናውን በራሳቸው አቅም የመሥራት ብቃትን ነው። አዎ፣ ከዚህ በፊት በነበረ እጅግ አሳፋሪና ኢ-ሙያዊ አሰራር ምክንያት ተማሪዎችን አንዱን ካንዱ፣ ሰነፉን ከጎበዙ ሁሉ መለየት እስኪያቅት ድረስ ነገሮች ተደበላልቀው እንደነበር ይታወሳል።


በዚሁ መደበላለቅ ምክንያትም ተማሪዎች፣ በተለይም ተፈታኝ ተማሪዎች ነገር ዓለሙን እርግፍ አድርገው በመተው ሁሉ ነገራቸውን ኩረጃ ላይ አሳርፈው "እፎይ" ያሉበት ዘመን ነበር። ዩኒቨርሲቲዎች እምባ አውጥተው እስኪያለቅሱ ድረስ ስሙን ሁሉ የማይጽፍ ተማሪ እየተመደበላቸው ወደ "ሀሁ . . ." ማስቆጠር ደረጃ ወርደው እንደነበር ራሳቸው ሲናገሩ ያልሰማ ቢኖር ጥቂት ነው። እንደ ትምህርት ሚኒስቴር ሪፎርም ከሆነ በሂደት እነዚህ ሁሉ ችግሮች እየተፈቱ በመሄድ ላይ ናቸው። ትግሉ እልህ አስጨራሽ ቢሆንም፣ ሁሉም ሰው የሚተባበር ከሆነ ችግሩ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይፈታል ተብሎ ይጠበቃል።

ተፈታኝ ተማሪዎች በሚገባ ተዘጋጅተው ጥሩ ውጤት በማምጣት ወደ እሚቀጥለው የትምህርት እርከን (ፕሮግራም) መሻገር አለባቸው እየተባለ ነው። ትክክል ነው። ነገር ግን፣ ከዘንድሮ የ 2015ዓ.ም ተፈታኞችና ያጋጠሟቸው እድሎች አኳያ አንድ የታየ ልዩ አጋጣሚ ቢኖር ከፍተኛ ውጤት ያመጡ 1000 ተማሪዎች በመጀመሪያ ምርጫቸው በሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች የመመደባቸው ጉዳይ ነው።

አዎ፣ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንዲሉ፣ ከፍተኛ ውጤት ያመጡ 1000 ተማሪዎች የመጀመሪያ ምርጫቸው በሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ተመድበው ደስታቸውን እጥፍ ድርብ አድርገዋል። ይህ ተማሪዎቹ እራሳቸው ለራሳቸው ያስገኙት ድርብ ድል በመሆኑ ከመደሰትም አልፈው ሊኮሩ ይገባል። የዘንድሮ ተፈታኞችም ይህንን ልዩ እድል ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ይህ ልዩ እድልና አጋጣሚ ከእጃቸው እንዳያመልጥ በማሰብ ወገባቸውን ጠበቅ አድርገው በመሥራት ስኬታቸውን ድርብ ድርብርብ ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃልና ዓመቱ ልዩ ነው ማለት ይቻላል።

የዘንድሮውን ውጤት ተከትሎ፣ በሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘና እና ፈተናዎች ኤጀንሲ አማካኝነት "የዘንድሮው ውጤት ከአምናው ጋር ሲነፃፀር በቁጥርም በውጤትም የተሻለ" መሆኑ ("አስደንጋጭነቱ" እንዳለ ሆኖ) እንደተነገረው ሁሉ፤ በሚቀጥለው ዓመትም የዚሁ ዓይነት ("አስደንጋጭ" የሚለው በነጭ ተሰርዞ) አዲስ ዜና እንደሚነገር ተስፋችን ነው።

# «ኢትዮጵያ ጥንታዊ የሆነ የዲፕሎማሲ ታሪክ ያላት ሀገር ነች»



**-ኤመሬትስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ**

ስምስም መንግሥቱ

**ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲ ረጅም ታሪክ ያላት ሀገር ነች፡፡ በጥንታዊ፣ በመካከለኛው እንዲሁም በዘመናዊ የዲፕሎማሲ ታሪኳም በየዘመኑ በነበሩ መሪዎች የተለያዩ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ ይህ የዲፕሎማሲ ታሪክም ዛሬ ድረስ ቀጥሏል፡፡ ስመሆኑ ኢትዮጵያ ከድሮ እስከ ዘንድሮ በዲፕሎማሲ ረገድ ያላት ታሪክ እንዴት ይታያል ስንል በታሪክ ምርምር ዘርፍ ስመጥር የሆኑትን ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴን አነጋግረናል፡፡ መልካም ንባብ፡፡**

**አዲስ ዘመን፣ ከጥንት ጀምሮ ኢትዮጵያ ከሀገራት ጋር የነበራት የዲፕሎማሲ ግንኙነት ታሪክ ምን ይመስላል?**

**ፕሮፌሰር ባህሩ፣** የኢትዮጵያ የጥንት መገለጫ የአክሱም መንግሥት ሲሆን፣ የውጭ ግንኙነቱም በንግድና በኃይማኖት ላይ የተመሰረተ ነው። አክሱም ከዓለም ጋር በጣም ሰፊ የሆነ የንግድ ግንኙነት ነበራት። በተለይም ከሜዲትራኒያን ዓለም ጋር በጊዜው ሰፊ የንግድ ልውውጦች እንደነበሩ የታሪክ ሰነዶች ያሳያሉ፡፡

በወቅቱም በዓለም ውስጥ ዝነኛ ወይንም እውቅና ካላቸው ወደቦች መካከል አንዱ የሆነው አዶሊስ ወደብ ነበር፡፡ በተለይም አንድ በተጓዥ መልኩ የተጻፈ ዘገባ በዝርዝር እንደገለጸው ብዙ ሸቀጦች እንደሚገቡና በዚያውም ልክ ይወጡ እንደነበር። የንግድ ግንኙነቱ የኋላ የኋላ ደግሞ ለኃይማኖት ግንኙነት መሠረት ሆነ፡፡

በዚሁ መሠረት በኢዛና ዘመን፣ ከመካከለኛው ምሥራቅ ወይንም ከሜዲትራንያን የመጡ ሰዎች ንጉሱንም ቤተሰቡንም አጥምቀው የክርስትና ኃይማኖት በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ሊመሰረት ቻለ፡፡ በገዥው መደብ አካባቢ በዚህ መልኩ ከተፈጸመ በኋላ ደግሞ ከአንድ መቶ ዓመት በኋላ ወደ ሰፊው ሕዝብ ሊሰርጽ ችሏል፡፡ ምክንያቱም ተሳእቱ ቅዱሳን የሚባሉ፣ አሁን ቱርክና ሶሪያ ከሚባሉ አካባቢዎች የመጡ፣ እነርሱ ደግሞ በስፋት አቡነ ገሪማ፣ አቡነ ባታሊዮን የሚባሉ የክርስትና ኃይማኖትን ለማስፋፋት ቻሉ፡፡

የኃይማኖት ጉዳይ በስድስተኛው መቶ ዓመት በአጼ ካሌብ ዘመን አንድ አዲስ ምዕራፍ የታየበት ነበር። በዚያን ጊዜ በየመን አካባቢ የሚኖሩ ክርስቲያኖችን አንድ የየሁዲ ንጉሥ በጣም ያሰቃያቸውና ይጨቁናቸው ነበር፡፡ በወቅቱ የአክሱም መንግሥት በተለይም ቢዛንታይን ከሚባለው ጋር ጥብቅ ግንኙነት ስለነበረው ወደ 60 የሚሆኑ መርከቦችን ተልኮለት ይሰቃዩ የነበሩ ክርስቲያኖችን ለማዳንና የዩሁዲውን ንጉስንም ለማሸነፍ በቅቷል፡፡፣ ከዚያም አልፎ አብርሃም የሚባል እንደራሴ እዛው በማቆም ለተወሰነ ጊዜ በአስተዳደሩ ቁጥጥር ሥር ለማቆየት ችሏል፡፡

ስለዚህ የንግድ ግንኙነቱ ወደ ኃይማኖት ሊዞር ችሏል ማለት ነው፡፡ የኃይማኖት ግንኙነቱ በዚህም አላበቃም።እንደሚታወቀው የእስልምና ኃይማኖት በሚጀምርበት ጊዜ በወቅቱ የነበሩት የአካባቢው ገዢዎች ስልተቀበሉት ነብዩ መሃመድ የተወሰኑ ተከታዮቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ ወደ ሀበሻ ልከዋል።

‹‹ፍትህ የሚያውቅ ነው ንጉሥ ሀበሻ ምድር አለና እርሱ ጋር ሄዳችሁ ጥገኝነት ጠይቁ›› ተብሎ የመጀመሪያዎቹ ሙስሊሞች ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ነው በአክሱም ዘመን የመጨረሻው ዓመታት አካባቢ ነበር፡፡

በዛጉዌ ስርዎ መንግሥት ያን ያህል የጠበቀ የዲፕሎማሲ ግንኙነት አልነበረም፡፡የተገደበ ነበር። ግን ደግሞ እየሩሳሌም የሁሉም ክርስቲያኖች በተለይም የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች፣ አንድ መዳረሻ ነበረችና በዚህ አንዱ ትልቁ ነገር ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ የሚደረገው ጥረት ነበር፡፡

ብዙ ጊዜ ግብጾችንና ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችን የሚያጨቃጭቀው ዴር ሱልጣን ገዳም በዚህ ዘመን ለኢትዮጵያውያን እንደተሰጠ ነው የሚተረከው፡፡ ይበልጥ ግንኙነት የነበረው በመካከለኛ ዘመን ነው፡፡

ከ13ኛው መቶ ዓመት መጨረሻ ጀምሮ እስከ 16ኛው መቶ ዓመት ከአውሮፓ ጋር መልከ ብዙ ግንኙነት የተካሄደበት ጊዜ ነው፡፡

አውሮፓውያን በዚያን ጊዜ የመስቀል ጦርነት ያካሂዱ ነበር፡፡ በአውሮፓ ክርስቲያኖችና በሙስሊሞቹ መካከል የሚደረግ ጦርነት ነው የነበረው፡፡ ጦርነቱ እየተራዘመ በሄደ ቁጥር የአውሮፓ ነገሥታት የክርስቲያን አጋር መንግሥት ይፈልጉ ነበር፡፡

ቄስ ጆን የሚባል ኃይማኖተኛ የሆነ ገናና የክርስቲያን ንጉሥ አለ፤ እርሱን ማግኘት አለብን፤ እርሱን ካገኘን ሙስሊሞችን በሁለት አቅጣጫ ወጥረን ይዘን እናሸንፋቸዋለን፤ እኛ ከምዕራብ እርሱ ከምሥራቅ የሚል ትልቅ እምነት ነበራቸው፡፡

ቄስ ጆንን ለማግኘት ያልዳሰሱትና ያላሰሱት ቦታ አልነበረም፡፡ በመጨረሻ ግን ዓይናቸው እና ቀልባቸው ያረፈው ኢትዮጵያ ላይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በወቅቱ ገናና የሆነ የክርስቲያን ንጉሥ ስለነበራት፤ የአውሮፓና የኢትዮጵያ ግንኙነት በዚህ ላይ የተመሰረተ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ግን ይሄ ከአውሮፓውያን ብቻ ሳይሆን፤ በኢትዮጵያዊያንም በኩል ተነሳሽነቱ ወይንም እንቅስቃሴ ነበር ፡፡ አጼ ዳዊት የሚባለው ንጉሥ በ14ኛው መቶ ዓመት መጨረሻና በ15ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ ከአውሮፓውያኑ ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለመመሥረት ጥረት አድርጎ ነበር፡፡

ከዚያ በኋላም ተከታታይ ነገሥታት ልዑካንን ወደ አውሮፓ ይልኩ ነበር፡፡ አውሮፓውያኑ በብዛት የሚጠይቁት ንዋየ ቅዱሳን፣ ሙያተኞች ግንበኞች፣አናጢዎች፣ ጌጣጌጥና ልብሶች የመሳሰሉትን ነበር፡፡

በወቅቱም ከ10 በላይ የሚሆኑ ልዑካን ወደ አውሮፓ ሄደዋል፡፡ አውሮፓ ሲባል እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ ማለታችን አይደለም፡፡ ስፔን፣ ፖርቹጋልና ጣሊያን ናቸው፡፡ በዚያን ጊዜ ጣሊያን ውስጥ ቬኒስ የሚባል የታወቀ መንግሥት ነው የነበረው። እና ከነዚህ ሀገራት ጋር ግንኙነት ለመመስረትና ይጠይቋቸው የነበሩ ቁሳቁሶች እንዲሄዱላቸው በየጊዜው ልዑካን ይላኩ ነበር፡፡

በአንድ ወቅት እንደውም በአጼ ይሳቅ ጊዜ ከስፔን ነገሥታት ጋር በጋብቻ ለመተሳሰር ጥያቄ ቀርቦ ነበር። በርግጥ ለፍሬ አልበቃም፡፡ ግን ግንኙነቱ ጥልቀትና ስፋት ያለው እንደሆነ አመላካች ነው፡፡

የመካከለኛው ማሳረጊያ፤ በኢትዮጵያ በኩል ትልቅ ተነሳሽነት ተደርጎ የሚወሰደው ንግሥት እሌኒ የወሰደችው ርምጃ ነው፡፡ ንግሥት እሌኒ ማቲዎስ የሚባል መልእክተኛ ወደ አውሮፓ ልካ፤ ግንኙነት ለመመስረት ጥረት አድርጋለች፡፡ በዚያን ጊዜ ከሙስሊም ሱልጣኖች መንግሥታት ጋር የነበረው ውጥረትና ጦርነት እያየለ ሲመጣ፤ አጋር ያስፈልገኛል በሚል ወታደራዊ ግንኙነት ለመመስረት ንግሥት እሌኒ በ16ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ ልዑክ ላከች፡፡

ይሄን ተከትሎ አልቫሬስ የሚባል በታሪክ በጣም የሚታወቅ ቄስ፤ አባል የሆነበት በወቅቱም ትልቅ የሆነ የፖርቹጋል ልዑክ ወደ ኢትዮጵያ መጣ፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ትልቅ የሆነ የውጭ ሀገር ልዑክ ወደ ሀገር መጥቶ ግንኙነት ሲመሰርት የመጀመሪያው ነበር፡፡ ከዚያ የልዑክ መምጣት ጋር ተያይዞ ያተረፍነው ነገር ቢኖር አልቫሪየስ የጻፈው መጽሐፍ ነበር፡፡ (ዘ ፕሪስተርስ ኦፍ ዘ ኢንድ) የሚለው መጽሐፍ የወቅቱን ሁኔታ በአግባቡ ያስረዳል። ወደ ሀገሩ ሲመለስ የመካከለኛው ዘመን መንግሥት ከግራኝ አሕመድ ጦርነት በፊት ምን ይመስል እንደነበር ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ትልቅ የታሪክ ሰነድ ትቶልናል።

በዚህ የተጀመረው እንቅስቃሴ፤ በመጨረሻ የግራኝ አሕመድ ጦር፤ ጠቅላላ ኢትዮጵያን አዳርሶ እስከ ሰሜን ኢትዮጵያ ደረሰ፡፡ በመጨረሻም የንግሥት እሌኒ ጥያቄ መልስ አግኝቶ ወደ 400 የሚሆኑ የፖርቹጊስ ወታደሮች ለእርዳታ ወደ ኢትዮጵያ መጡ፡፡ በፖርቹጋል አጋዥነት የአሕመድ ግራኝ ጦር ተሸንፎ የክርስቲያኑ መንግሥት እንደገና ለማንሰራራት ቻለ፡፡

ድሉን መሠረት በማድረግም ኢየሱሳውያን የሚባሉ ካቶሊክ ሚሲዮናውያን በብዛት ወደ ኢትዮጵያ መጡ። የኦርቶዶክስ ኃይማኖትን በማስቀየር ኢትዮጵያን ካቶሊክ ለማድረግ እንቅስቃሴ ጀመሩ፡፡ እንደውም ንጉሡን ካቶሊክ ለማድረግ ባደረጉት እንቅስቃሴም ተሳካላቸው፡፡ አጼ ሲንሲዮስ የካቶሊክ እምነት ተቀበሉ። ወደ ሕዝቡም ለማስረጽ ሲፈልጉ ነበር የእርስ በርስ ጦርነት የተከተለው። ጦርነቱ ካቶሊክ ትሆናላችሁ፤ አንሆንም በሚል የተቀሰቀሰ ሲሆን በወቅቱም በጦርነቱ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ አለቀ፡፡

በመጨረሻ ግን ንጉሡ በመጸጸት ‹‹መስሎኝ ነበር›› በማለት ዙፋኑን ለልጁ ፋሲለደስ ለቀቀለት። እርሱ ዙፋኑን ከለቀቀ በኋላም የቀድሞ ሥርዓት ተመለሰ፡፡ አጼ ፋሲለደስ ከነገሡ በኋላ መጀመሪያ የወሰደው ርምጃ ኢየሱሳውያንን ከኢትዮጵያ ማስወጣት ነበር፡፡

ከአውሮፓውያን ጋር የተጀመረው ግንኙነት ብዙ ጣጣ እያመጣ ነው በሚል ኢትዮጵያ ከአውሮፓ ጋር ያላት ግንኙነት መቋረጥ እንዳለበት ወሰነ፡፡ በዚህም ኢትዮጵያና አውሮፓ ለ200 ዓመታት ሳይገናኙ ቀሩ፡፡ አጼ ፋሲለደስ እንደውም ከሙስሊም ባለሥልጣኖች ጋር የመቀራረብ ፖሊሲ ነበር የሚከተለው፡፡

አውሮፓውያን በ19 መቶ ዓመት ነው እንደገና በአዲስ መንፈስ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን፤ በጠቅላላ አፍሪካ በኃይማኖት፣ በንግድና በዲፕሎማሲ ከፍተኛ ዘመቻ በማድረግ ወደ አፍሪካ ለማቅረብ የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስ200 ዓመት ከአውሮፓ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አልተደረገም ማለት ነው?**

**ፕሮፌሰር ባህሩ፡-** አልፎ ከሚመጡ ተጓዦችና ጸሐፍት በስተቀር ከ200 ዓመት በፊት እንደነበረው እዚህ ግባ የሚባል ግንኙነት አልነበረም፡፡ ደብዘዝ ያለ ግንኙነት ነው የነበረው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በየዘመናቱ የነበሩ ነገሥታት ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ለማድረግ ያደረጉት ጥረት ምን ይመስላል?**

**ፕሮፌሰር ባህሩ፡-** ሁሉም ነገሥታት የባህር በር ጉዳይ ዋነኛው አጀንዳቸው ነበር ማለት ይቻላል፡፡ አጼ ቴዎድሮስ እንደሚታወቀው ሁለት ዓላማ አንግበው ነበር የተነሱት፡፡ አንዱ ተከፋፍላ የነበረችውን ኢትዮጵያ አንድ በማድረግ ተዳክሞ የነበረውን የንጉሡ ነገሥት ሥልጣን መልሶ ለማደስ ነበር፡፡ ሁለተኛው ኢትዮጵያን ለማዘመን ነው፡፡ በተለይ ኢትዮጵያ እንድትዘምን ቁርጠኝነቱ ከፍተኛ ስለነበር ከፈረንጆቹ ጋር መወዳጀት ጀመሩ፡፡ እንደ አጋጣሚ ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ሁለት እንግሊዛውያን ቤንና ፕራውደን የሚባሉ ወዳጅ ሆነዋቸው ነበር፡፡

በነዚህ እንግሊዛውያን አማካኝነት የአውሮፓን እርዳታ አግኝቼ ኢትዮጵያን አዘምናለሁ የሚል ከፍተኛ እምነት ነበራቸው፡፡ በዚህ መካከል ነበር ያ ጣጠኛ የተባለውን ደብዳቤ እኤአ በ1862 ለንግሥት ቪክቶሪያ የላኩት፡፡ ለላኩት ደብዳቤ መልስ ሳያገኙ ቀሩ፡፡ በዚያም ተናድደው ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን ፈረንጆች አገቱ፡፡ እንግሊዞችም የታገቱትን ለማስፈታት በናፒር የሚመራውን ጦር ላኩ፡፡ አጼ ቴዎድሮስም እጄን አልሰጥም በሚል እራሳቸውን ሰዉ፡፡

በአፄ ቴዎድሮስም ሆነ በአፄ ዮሐንስ ዘመን የምናየው ነገር የዋህነት ነበር፡፡ እኛም እነርሱም ክርስቲያን ነን፣ ክርስቲያን ለክርስቲያን ደግሞ ማገዙ አይቀርም የሚል እሳቤ ነው የነበራቸው፡፡ ስንጠይቃቸው ይረዱናል የሚል እምነት ነበራቸው። ሁልጊዜም በቱርኮች ተከበናል የሚል ስጋት አዘል ደብዳቤ ለአውሮፓ መንግሥታት ይልኩ ነበር።

ቱርክ የሚሉት ግብጽን ነበር፡፡ ተከብቤያለሁና ለመግዛት አልቻልኩም፤ እናንተም ክርስቲያን ሲጠቃ እንዴት ዝም ብላችሁ ትመለከታላችሁ ነበር የሚሉት። እነርሱም ክርስቲያን ስለሆኑ ይረዱናል የሚል እሳቤ ነበራቸው፡፡ አፄ ዮሐንስም ይህንኑ ነበር የሚደግሙት። በዲፕሎማሲ ዓለም ትንሽ የዋህነት ነበራቸው፡፡ የውጭዎቹ መንግሥታት በኃይማኖት ሳይሆን በጥቅም ነው የሚመሩት፡፡ ምን እጠቀማለሁ እንጂ በኃይማኖት አንድ ስለሆንን እናግዛለን የሚሉ አልነበሩም፡፡

በአጼ ዮሐንስ ዘመን ኢትዮጵያ ስለተከበበች በርካታ ደብዳቤዎችን ለእንግሊዞች ይጽፉ ነበር። እርሳቸው ትኩረታቸውን የሳበውና ለጦርነትም መንስኤ የሆነው የግብጽ መስፋፋት ፖሊሲ ነው። ግብጾች ሙስሊም ስለሆኑና እኛ ክርስቲያን ነን በሚል ግብጽን ለመቋቋም አውሮፓውያን ይረዱኛል የሚል ነበር፡፡ በዘመኑ የነበረው የዲፕሎማሲ ስሌት እንደዚያ አልነበረም፡፡ በወቅቱ ጦርነት ሁለት ጊዜ ተካሂዶ የነበረውን ጦርነት በመዋጋት ግብጾችን ማሸነፍ ችለዋል፡፡ በመጨረሻም ድሉን መሥመር ለማስያዝ በተለይም የባህር በር ለማግኘት፤ ከእንግሊዞች ጋር ያልሆነ ውል ተዋዋሉ፡፡

እኤአ 1884 የዓድዋ ስምምነት ተደረገ። በዚህ ወቅት የማህዲስቶች ንቅናቄ ሱዳንን አጥለቅልቀዋታል፡፡ ማህዲስቶች ሱዳንን ይገዙ ነበር። በወቅቱ ብዙዎች ግን ተሸንፈው በካምፕ ውስጥ ተከበው ነበር እንዲቀመጡ የተደረገው፡፡ በዚያ በኩል ወደ ግብጽ መሄድ ስለማይችሉ፤ በኢትዮጵያ በኩል እንዲወጡ አፄ ዮሐንስ ድጋፍ እንዲያደርጉ፤ በልዋጩ ደግሞ እንግሊዞች ነፃ ወደብ ምጽዋን ሊሰጧቸው ነበር ስምምነቱ፡፡

እኤአ 1884 የዓድዋ ስምምነት ከተፈረመ በኋላ እንግሊዞች ቃላቸውን መጠበቅ አልቻሉም። አጼ ዮሐንስ የገቡትን ውልም አክብረው እስከ መጨረሻው ድረስ በመሄድ ግብጾቹን በራስ አሉላ አማካኝነት፤ ከተከበቡበት አውጥተው በኢትዮጵያ በኩል ወደ ሀገራቸው እንዲሄዱ ወይንም እንደመለሱ አደረጉ፡፡

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# «ኢትዮጵያ ጥንታዊ የሆነ የዲፕሎማሲ...

ከ ገጽ 9 የዞረ



በእንግሊዞች በኩል ግን የተገባው ቃል አልተከበረም፡፡ ወይንም ምንም ነገር አልተደረገም፡፡ ነፃ ወደብ የማግኘት ነገር አልተተገበረም።

አፄ ዮሐንስ ከማህዲስቶች ጠላትነትን ነው ያተረፉት፡፡ «በማህዲስቶቹ በኩል የነበረው የጠላቴ ወዳጅ ጠላቴ ነው የሚል ነበር» ግብጾቹ በኢትዮጵያ ንጉሥ በአፄ ዮሐንስ አማካኝነት በራስ አሉላ እርዳታ ነው ያመለጡት፡፡ ስለዚህ ፍልሚያቸን ከኢትዮጵያ ጋር ነው ብለው፤ለተከታታይ አራት አመታት በኢትዮጵያና በማህዲስቶች መካከል ውጊያ ተካሄደ። በመጨረሻ አፄ ዮሐንስ መተማ ላይ ተሰዉ። ስለዚህም የኢትዮጵያ መንግሥታት ይከተሉት የነበረው የዲፕሎማሲ አካሄድ የዋህነት የተሞላበት ነበር ማለት ይቻላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የባህር በር ለማግኘት የተደረጉ ጥረቶች ምን ይመስሳሉ?**

**ፕሮፌሰር ባህሩ፡-** የአፄ ምኒልክ ጉዳይም ቢሆን፤ ያለፉት ተቀጽላ ነው፡፡ የባህር በር የማግኘት ጉዳይ አንገብጋቢ ጥያቄ ነበር፡፡ እኤአ በ1883 አንድ በጣም ዝነኛ የሆነ ሰልኩላር ለአውሮፓ ነገሥታት በሙሉ ይጽፋሉ፡፡ በዚህ የነበረው ጥረት የኢትዮጵያ ዳር ድንበር ይህ ነው ብሎ ለማሳወቅ ነው፡፡ ይህን የሚያደርጉትም አውሮፓውያን እየተስፋፉ ስለሆነ እነርሱ መጥተው ከማጥለቅለቃቸው በፊት እኔ ግዛቴ ይሄ ነው ብዬ ላሳውቃቸው ብለው ሰፋ ያለ ሃሳብ በመያዝ ለዓለም መንግሥታት በሙሉ ሰርኩላር በትነዋል፡፡ በመጨረሻ ሁሉም መንግሥታት ኢትዮጵያ የባህር በር እንድታገኝ እንዲረዱቻቸው ተማጽነዋል፡፡

ዳግማዊ ምኒልክ ከአብዛኞቹ መንግሥታት ጋር ጥሩ ግንኙነት ነበራቸው፡፡ ከጣሊያን ጋር ግን አይዋደዱም ነበር፡፡ አንድም ከአፄ ዮሐንስ ጋር በነበራቸው የስልጣን ሽሚያ፤ የነርሱን አጋዥነት ስለፈለጉ፤ ከእነርሱ ጋር በመቀራረብ ውል መዋዋል ጀመሩ፡፡ አሁን ሰው የውጫሌ የውል ስምምነትን ብቻ ነው የሚያውቀው፤ ነገር ግን ከዚያ በፊት፤ አንድ ሁለት ውሎች ተዋውለዋል። አውሮፓውያን ሲመጡ የንግድና የወዳጅነት ውል የሚል ስላላቸው በ1930ዎቹና በ1940ዎቹ አካባቢ የተለያዩ ውሎች ነበሩ፡፡ አፄ ምኒልክ በዚህ መልኩ ሁለት ውሎችን ተዋውለው በመጨረሻ ደግሞ የውጫሌን ውል ተዋዋሉ፡፡ የውጫሌውን ውል ደግሞ በርካታ ጦሶችን ይዞ መምጣቱ የሚታወቅ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ዓድዋ ላይ የተቀዳጀችው ድል ለውጭ ግንኙነት ፖሊሲዋ ያለው አበርክቶ እንዴት ይገለጻል?**

**ፕሮፌሰር ባህሩ፡-** የዓድዋው ድል ሁሉን ነገር ነው የለወጠው፡፡ ከዓድዋ በፊት፤የአውሮፓውያን ፍላጎት፤ እምነትም ሊባል ይችላል አፍሪካን በሙሉ በቁጥጥራችን ሥር እናደርጋለን የሚል ነበር የነበረው፡፡

በጀርመናዊው ቢዝማርክ አስተናባሪነት የበርሊን ኮንፈረንስ ከሚባለው እኤአ 1885 በአውሮፓ፤ ካደረጉት ስምምነት ጀምሮ ወደ አፍሪካ በስፋት እየገቡ መከለል ጀመሩ፡፡ ባንዲራ መስቀል እና አገዛዛቸውን ማጠናከር ጀመሩ፡፡ ጣሊያንም በዚህ ስሌት ነው ወደ ኢትዮጵያ መስፋፋት የጀመረችው፡፡ በመጀመሪያም ኤርትራን ያዘች። ኤርትራ የሚለውን ስያሜም በ1890 የሰጠችው ጣሊያን ናት፡፡ ኤርትራ ቀደም ሲል መረብ ምላሽ ነበር ተብላ የምትጠራው፡፡

ኤርትራን እንደ መፈናጠጫ ነበር የተጠቀመችው፤ ምክንያቱም ዋናው ሀብት ያለው ኢትዮጵያ ስለሆነ፤ ቀስ በቀስ እየሸረሸረች ወደ ዓድዋ ጦርነት ውስጥ እንዲገባ አደረገች፡፡ ዓድዋ ላይ የተደረገው ጦርነት በድል መጠናቀቁ፤ አውሮፓውን የነበራቸውን ምኞት ሙሉ በሙሉ ቀይሮታል፡፡

በተከታታይ በተደረጉ ጦርነቶች ኢትዮጵያ በቅኝ እንደማትገዛ ከአንዴም ሁለቴም አረጋገጠች። ከዚያ በኋላ ያለው አማራጭ አንደኛው በአቻነት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መመስረት ነው፡፡ ያኔ ለጋሲዮን ነበር የሚባለው። ለጋሲዮን ማቋቋም ሲሆን፤ በአንድ ዓመት ውስጥ ሶስት ለጋሲዎች ተቋቋሙ፡፡ በጣም የሚገርመው፤ ከዓድዋ ድል በኋላ በዓመቱ መጀመሪያ የተቋቋመው የጣሊያን ለጋሲ ነበር፡፡ ሁለተኛ ፈረሳይ፣ ሶስተኛ እንግሊዝ ነበሩ፡፡ በሂደት እነ አሜሪካን፣ ጀርመን መጡ፡፡

ኢትዮጵያ በዓድዋ ላይ ድል መቀዳጀቷ ከአሁን በኋላ ኢትዮጵያን ቅኝ መግዛት አንችልም፤ ያለን አማራጭ ጥቅማችንን ማስከበር፣ ጤናማ የሆነ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ማቋቋም ነው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ኢትዮጵያ አሁንም የበለጠ መስፋፋት ስለምትችል መገደብ አለባት፤ ለመገደብ ደግሞ ሁነኛው ዘዴ ድንበር ማካለል ነው የሚል ውሳኔ ላይ ደረሱ፡፡

ከዓድዋ ድል በኋላ እንደዚሁ በዓመቱ ጀምሮ የድንበር ማካለሉ ሥራ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ተከናውኖ የኢትዮጵያ ድንበሮች በሙሉ ተካለሉ። ከኤርትራ፣ ከሱዳን፣ ከጅቡቲ ጋር የመጀመሪያው ድንበር የማካለል ሥራ ተከናወነ፡፡ ከሶማሊያና ከኬንያ ጋርም ቀጠለ፡፡

የሶማሊያው ከጣሊያን ጋር፣ የኬንያው ደግሞ ከእንግሊዝ ጋር በመሆን ነበር የማካለል ሥራው የተከናወነው፡፡ ኢትዮጵያ ከ10 ዓመት በኋላ ያላትን ቅርጽ የምናየው በዚህ መልኩ ነው፡፡ የድንበር ቅርጽ የያዘው ይሄኔ ነው፡፡

ሆኖም ዓድዋ ትልቅ ድል አንፀባራቂ የሆነውን ያህል፤ ኤርትራን ማስመለስ ባለመቻሉ፤ ወደብ አልባ ሆና ቆየች። ስለዚህ የወደብ ማጣት፣ አፄ ምኒልክ እየተዳከሙ በሚሄዱበት ጊዜ ኢትዮጵያ ትፈርሳለች ከአፄ ምኒልክ በኋላ አትቆይም የሚል ሃሳብ ስለነበራቸው እንዴት አድርገን እንቀራመታለን የሚል ውል እስከመዋዋል ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡

ምኒልክ ከሞቱ በኋላ እያንዳንዳቸው ይሄ የኔ ይሆናል እስከ ማለት ደርሰው ነበር፡፡ የሶስትዮሽ ውል እኤአ 1906 እንግሊዞች ድንበራቸው አካባቢ፣ ጣሊያኖችም እንዲሁ በሁለት በኩል ድንበራቸውን ተከትለው፤ ፈረንሳዮች የባቡር ሃዲድ ተከትለው ያለውን ግዛት እንደሚወስዱ ነው የተዋዋሉት፡፡

ይህንኑ እውን ለማድረግ ከጊዜ በኋላ ደግሞ ኢትዮጵያ ላይ የመሣሪያ ማዕቀብ ጣሉ፡፡ የመሣሪያ ማዕቀብ ጠንቅ የታወቀው፤ ሞሶሎኒ እስከአፍጢሙ ታጥቆ ሲመጣ ነበር። በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ በማዕቀቡ ምክንያት መሳሪያ ማስገባት ስለማትችል እስከአፍጢሙ የታጠቀውን የጣሊያንን ጦር የመመከት አቅም አልነበራትም፡፡ ሆኖም በባዶ እጅም ቢሆን ለአምስት ዓመታት በዱር በገደሉ በተደረገ መስዋዕትነት ኢትዮጵያን ማትረፍ ተችሏል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአፄ ምኒልክ ዘመን ከአሜሪካን፣ ፈረንሳይና ሩሲያ ጋር የነበረው ግንኙነት ምን ይመስል ነበር?**

**ፕሮፌሰር ባህሩ፡-** በመቻቻል ነው ያሳለፉት ማለት ይቻላል፡፡ እነርሱ ኢትዮጵያ ውስጥ ሌጋሲዮኖች አሏቸው በዚያ አማካኝነት ጥቅማቸውን ያስከብራሉ። ለምሳሌ ፍርድን በተመለከተ ልዩ ፍርድ ቤት ነበር፤ የውጭ ዜጎች በልዩ ፍርድ ቤት ነበር የሚዳኙት፡፡ ዳኞቹ ግን ኢትዮጵያውያን ነበሩ። የቆንሲሎቻቸው ተወካዮች በሚገኙበት ነበር ፍርድም የሚሰጠው፡፡ ከዚህ በተረፈ ግን ሙሉ ለሙሉ የአቻ ግንኙነት ነበር ማለት ይቻላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ከአሜሪካን ጋር የንግድ ግንኙነት ነበራት?**

**ፕሮፌስር ባህሩ፡-** የንግድ ስምምነት እኤአ በ1903 ነበር የተጀመረው፡፡ ግን ከንግድ ውጭ ብዙም ግንኙነት አልነበራቸውም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ሌጋሲዎን እንኳን ያቋቋሙት በጣም ዘግይተው ነው። አሜሪካውያኑ ጉዳያቸውን ሲከታተሉ የነበረው ከኤደን ነበር፡፡ በኋላ ላይ የፍትሃ ኃብተጊዮርጊስ ግቢ የነበረው አሁን አሜሪካን ግቢ የሚባለውን ተከራይተው አቋቋሙ፡፡ ንግዱን ብቻ የማበረታታት እንጂ ዲፕሎማሲው እንደነእንግሊዝ፣ ጣሊያንና ፈረንሳይ የጎላ ተሳትፎ አልነበራቸውም ማለት ይቻላል፡፡ የነርሱ ተሳትፎ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ነው የሚመጣው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በዓድዋው ጦርነት ሩሲያ ድጋፍ አድርጋለች የሚባል ነገር አለ፡፡ ድጋፉ ምን ነበር?**

**ፕሮፌሰር ባህሩ፡-** ሩሲያ ድጋፍ ያደረገችው ቀይ መስቀል በመላክ እና ቁስለኞችን በመንከባከብ ነበር። ያ ድጋፍ አድጎ መሠረቱ ደጃዝማች ባልቻ ሆስፒታል ለመመስረት በቃ፡፡ የዲፕሎማሲ እንጂ የመሣሪያ ድጋፍ ግን አልነበረም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በልጅ እያሱ እና በንግሥት ዘውዲቱ ዘመን የነበረው የዲፕሎማሲ ግንኙነት ምን መልክ ነበረው ?**

**ፕሮፌሰር ባህሩ፡-** ልጅ እያሱ ኢትዮጵያ በኃያላን መንግሥታት ሥር እንዳትውደቅ፤ከሁሉም ጋር ግንኙነት እንዲኖራት ማድረግ የሚለውን የአፄ ምኒልክን ፖሊሲ ነው የተከተሉት፡፡ በኋላ ላይ ግን በመጥፎ ተተረጎመባቸው። በተለይ ከጀርመን ጋር የነበራቸው ግንኙነት ጠበቅ ስላለ በአንደኛው የዓለም ጦርነት የጀርመንና የቱርክ ደጋፊ ናቸው ተብለው ተፈረጁ። በዚህም ምክንያት ፈረንሳይ፣ እንግሊዝና ጣሊያን አብረው አብረው ከውስጥ ካሉት ጋር የፀረ ኢያሱ ኃይሎች ጋር በመተባበር ሊያስወግዷቸው የቻሉት። ግን ከጊዜ በኋላ የወጡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት እርሳቸው ወደዚያ ካምፕ አልገቡም፡፡

እንደሚባለውም አልሰለሙም፡፡ እኔም አልሰ ለምኩም፣ ሕዝቡም እንዲሰልም አልፈልግም፣ ሲሉም በግልጽ ተናግረዋል፡፡ እድሊፕ የሚባል አንድ የቅርብ ወዳጃቸው የሕይወት ታሪካቸውን በጻፈው መጽሐፍ ላይ በደንብ አድርጎ እንደገለጸው፤ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ላይ ማን ቢያሸንፍ ይሻልሀል ወይንም ትመርጣለህ ሲባል እንደ እውነቱ ከሆነ ሁሉም ጦርነት ቢራዘምና ሁሉም ቢዳከሙ ነው የምመርጠው ብለው የተናገሩት አለ፡፡ ኢትዮጵያ የማንም ጥገኛ ሳትሆን ተቻችላ እንድትቀጥል ነበር ፍላጎታቸው፡፡

ንግሥት ዘውዲቱ በውጭ ጉዳይ አመራር ውስጥ አይገቡም ነበር፡፡ አልጋ ወራሹ ራስ ተፈሪ በኋላ አፄ ኃይለሥላሴ የተባሉት ነበሩ የሚመሩት፡፡ አንዱ ትልቁ ነገር የነበረው ከምዕራባውያን መንግሥታት ጋር ያላቸውን ግንኙነት የማጠናከር ጉዳይ ነው። ሁለተኛ ደግሞ ኢትዮጵያ በነፃ መንግሥትነቷ ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኝ ጥረት አድርገዋል። የመጀመሪያውን በተመለከተ የአንደኛው የዓለም ጦርነት እንዳለቀ፤ በራስ ናደው አባወሎ የሚመራ ልዑክ ወደ አሸናፊዎቹ ኃያላን መንግሥታት የእንኳን ደስ ያላችሁ መልእክት ተልኳል፡፡ ከዚያ ግን ዋናው ወሳኙ፣የተባበሩት መንግሥታት ነው፡፡

ያኔ የተባበሩት መንግሥታት የሀገራት የመንግ ሥታት ማህበር ነው የነበረው፡፡ ሊግኦፍኔሽን ውስጥ ኢትዮጵያን ለማስገባት በርካታ ተጋድሎ ተደርጓል። በተለይ እንግሊዞች ኢትዮጵያ ውስጥ የባርነት ንግድ ስለሚካሄድ ኢትዮጵያ አባል መሆን የለባትም የሚል ከፍተኛ ተቃውሞ ነበር፡፡ በወቅቱም ከጣሊያን በበለጠ ነበር እንግሊዞቹ የተቃወሙት። ሆኖም በከፍተኛ ትግል ኢትዮጵያ አባል ልትሆን ችላለች፡፡ በ1923 ነበር አባል የሆነችው፡፡

በርግጥ ይሄ አባልነት ምን ጠቀማት የሚለው ሌላ ጥያቄ ነው፡፡ የቁርጡ ቀን ሲመጣ ኢትዮጵያን ሊረዱ አልሞከሩም፡፡ አንድ የማህበር አባል ሌላኛውን የማህበር አባል በኃይል ሲያጠቃ እነርሱ አቋም መውሰድ ነበረባቸው፤ ግን አልቻሉም፡፡

ከጣሊያን መውጣት በኋላ የኢትዮጵያ እና አውሮፓውያን ግንኙነት ሁለት ምዕራፎች ነው የነበሩት። የመጀመሪያው፤ እንግሊዞች ብዙውን ነገር ኢትዮጵያን በኃይል የሚቆጣጠሩበት አካሄድ ነው የነበረው። ይሄን የሚያደርጉት ደግሞ ጣሊያንን ለማስወጣት የተጫወቱትን ሚና እንደውለታ በመቁጠር ነው፡፡እንደውም ኢትዮጵያ ከማለት ይልቅ በጠላት ተይዞ የነበረ ግዛት አስተዳደር የሚል መስርተው ነበር፡፡ በዚሁ ምክንያትም ኢትዮጵያ ነጻነቷን ለማወቅ ብዙ ጊዜ ፈጅቶባቸዋል፡፡

እኤአ በ1942 ከአፄ ኃይለሥላሴ ጋር ያደረጉት ስምምነት፤ ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ በእነርሱ መዳፍ ሥር የሚያስገባ ነበር፡፡ ባቡሩም፣ ፋይናንሱም፣ ወታደሩን ሁሉ በእነርሱ ቁጥጥር ሥር የሚያስገባ ነው። ከዚያ በኋላ እኤአ በ1944 ይህንን የሚያለዝብ እና የኢትዮጵያን ነፃ መንግሥትነት የሚያረጋግጥ አካሄድ ለመፍጠር ተችሏል።

ይሄ በአጠቃላይ ሲሆን በዝርዝር ሲታይ ደግሞ ኤርትራና ኦጋዴንን ለማስመለስ፤እንግሊዞች እንቅፋት ፈጥረው ነበር፡፡ ኤርትራ ውስጥ ኢትዮጵያን አንፈልግም የሚሉትን በመደገፍ፤ የአንድነት ኃይሉን በማዳከም ሚና ተጫውተዋል፡፡ኦጋዴንንም ከብዙ ትግል በኋላ ነው ማስመለስ የተቻለው፡፡ እንግሊዞች ታላቋ ሶማሌ የሚለውን መርዘኛ ሃሳብ ጥለው ነው የሄዱት፡፡

ከእንግሊዞች በኋላ ከአሜሪካኖች ጋር የተሻለ ግንኙነት ለመፍጠር ተሞክሯል፡፡ወታደሩ ትጥቁን የሚያገኘው ከአሜሪካኖች ነበር፡፡ በትምህርቱም፣ በወባ መከላከልና በሌላውም ግንኙነቱ እኤአ 1965 አካባቢ ድረስ የቀጠለ ነበር፡፡ በኋላ ላይ ግን አሜሪካኖቹ ገሸሽ እያሉ በመምጣታቸው የኢትዮጵያ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ እየቀነሰ ስለመጣ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አጠቃላይ በኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ታሪክ የተሻለ የሚባለው በየትኛው ዘመን ነበር?**

**ፕሮፌሰር ባህሩ፡-** የተሻለ ብሎ ለመምረጥ ከባድ ነው፡፡ ግን የአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ስኬት ያለበት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ብዙዎች ሲታገሉ የነበረው የባህር በር ጉዳይ ለአጭር ጊዜም ቢሆን መፍትሔ ያገኘው በእርሳቸው ዘመን ነው፡፡ አፄ ምኒልክ በተወሰነ ደረጃ ተሳክቶላቸው ነበር፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡኝ ሰፊ ማብራሪያ አመሰግናለሁ**

**ፕሮፌሰር ባህሩ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ተወዳዳሪነታቸው እየጨመረ የመጣው የሀገር ውስጥ የቆዳ ውጤቶች

**ወርቅነሽ ደምሰው**



የኢትዮጵያ የቆዳ ምርቶች በዓለም ገበያ ተቀባይነታቸው እየጨመረ እንደሆነ ይነገራል፡፡ በተለይ ከቆዳ የሚሰሩ ቦርሳዎች በዓለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪ ሆነው መቅረባቸው ተመራጭ እያደረጋቸው መሆኑን በዘርፉ የተሰማሩ አምራቾች ይጠቁማሉ። የሀገር ውስጥ የቆዳ ምርቶች ጥራታቸውን ጠብቀው መመረታቸው በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ መሆን እያስቻላቸው መሆኑን ያመላክታሉ።

በሀገር ውስጥ የቆዳ ውጤቶች ከሚያመርቱት ድርጅቶች “የአስ ኢትዮጵያ” (AS Ethiopia) የቆዳ ምርቶች አምራች ድርጅት አንዱ ነው፡፡ የድርጅቱ የፕሮዳክሽን ማናጀር አቶ ተስፋዬ በየነም የሀገር ውስጥ የቆዳ ምርቶች በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ መሆናቸውን ይመሰክራሉ፡፡ እሳቸው እንደሚሉት፤ ድርጅቱ በአብዛኛው የሴት ቦርሳዎችን ያመርታል፡፡ ቦርሳዎቹ ውበታቸውንና ጥራታቸውን የጠበቁ በምርጥ ዲዛይን የተሰሩ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ከውጭ ሀገር ከሚመጡት ቦርሳዎች ጋር መወዳደር እንደሚችሉም ገልጸዋል፡፡

የአስ ኢትዮጵያ ምርቶች በሀገር ውስጥ ገበያ ሰፊ ተቀባይነት እያገኙ መሆናቸው የሚናገሩት አቶ ተስፋዬ፤ ምርቶቹ ከዚህ ቀደም በገበያ ላይ ያልተለመዱና ለየት ያሉ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡ ህብረተሰቡ ምርቶቹን በጥራትና በይዘታቸው እንደሚወዳቸውና ፈልጎ እንደሚገዛቸውም ነው የተናገሩት፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ ድርጅቱ ወደዚህ ሥራ ከገባ ገና አንድ ዓመቱ ነው፤ ምርቶቹን ለሀገር ውስጥ ገበያ እያቀረበ ሲሆን፣ አሁን ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ ያለው ምርቶቹን ለውጭ ገበያ በመላክ ተቀባይነት ለማግኘት ነው፡፡ ምርቶችን ለውጭ ገበያ የመላኩ ሂደት ተጀምሯል፡፡

በቆዳው ዘርፍ ላይ የረጅም ጊዜያት ልምድ እንዳላቸው የሚናገሩት አቶ ተስፋዬ፤ ድርጅቱ ከዚህ በፊት እንደዚህ ዓይነት የሴቶች ቦርሳዎችን አምርቶ እንደማያውቅና ይህ የመጀመሪያ መሆኑን ያነሳሉ፡፡ እነዚህ ምርቶች መሥራት ሲጀምር ፋብሪካ አቋቁሞ በሰፊው ወደ ሥራ እንደገባ ጠቅሰው፤ በምርቶቹ በጥራትም ሆነ በተወዳዳሪነት ምንም የማይወጣለቸው እንደሆነ ይገልጻሉ። በተለይ ከተለያዩ የውጭ ሀገራት በተለያዩ አጋጣሚዎች ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ሰዎች በደንብ ወደው የሚገዟቸው መሆናችን ተናግረዋል፡፡

የቆዳ ምርቶታቸው በኅብረተሰብ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት ከፍተኛ ከመሆኑ በላይ እነዚህ ምርቶች ‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ ነው የተመረቱት›› የሚል ጥያቄ እያስነሳ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ተስፋዬ፤ ምርቶቹ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመመረታቸው ‹‹በኢትዮጵያ ተመረቱ/ made in Ethiopia/ የሚል ጽሑፍ እያስገቡ እንደሚሰራም ነው ያስታወቁት፡፡›› ‹‹በኢትዮጵያ የተመረተ›› መባሉ ምርቶቹ ኢትዮጵያ ውስጥ የተመረተ መሆኑ እንዲታወቅና ችግር ካለበት ችግሩ እዚሁ እንዲፈታ የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው፤ ዋናው ነገር ጥራት ያላቸውን ምርቶች አምርቶ ሀገርና ራስን ማስተዋዋቅ እንደሚቻል ማሳየት ነው ብለዋል፡፡

‹‹የሴቶች ቦርሳዎችን በተለያዩ ዲዛይኖችና ቀለሞች ዘመኑን በሚመጥን መልኩ ዘመናዊ አድርጎን መሥራት የቻልንበት ዋንኛ ምክንያት በገበያው ላይ ያሉ ክፍተቶችን አጠንተን ወደ ሥራ በመግባታችን ነው›› ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ ምርቶቹ በገበያው ያሉትን ክፍተቶች ሊሟሉ የሚችሉ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ የፋሽን ኢንዱስትሪውን ለማነቃቃትም የራሳቸው አስተዋጽኦ እንደሚኖራቸው አመላክተዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ የድርጅቱ የሴቶች ቦርሳዎች ዋጋቸውም ተመጣጣኝ ነው፤ ከ5ሺ ብር ጀምሮ እስከ 20ሺ ብር ይጠየቅባቸዋል፡፡ የቦርሳዎቹ ጥራት የዓለም ገበያ ስታንዳርድ የሚያሟሉ በመሆናቸው የሚወጣባቸው ወጪ ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ ዋጋቸውም ከዚያ አንጻር የተተመነ መሆኑን ተናግረዋል፡ ፡

ለቆዳ ምርቶች ሥራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ቆዳውና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች በአብዛኛው በሀገር ውስጥ እንደሚገኙ አቶ ተስፋዬ ጠቅሰው፤ እንደ መለዋወጫ ሌሎች ግብዓቶች ከውጭ እንደሚመጡ ገልጸዋል፡፡ ይህ ሁኔታም የቆዳ ምርቶችን በስፋት ለማምረት በሥራቸው ላይ እንቅፋት መሆኑን ይናገራሉ፡፡ በአብነት ጠቅሰው እንዳብራሩት፤ አንድ ቦርሳ ለመሥራት በርካታ መለዋወጫዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ እነዚህ መለዋወጫዎች ኢትዮጵያ ውስጥ አይመረቱም፤ አይሰሩም። ሁሉም ከውጭ የሚመጡ ናቸው፡፡ ከጉምሩክ ጀምሮ ያለው ሂደትም በጣም አሰልቺና ጊዜ የሚወስድ ነው፤ ይህ ሁሉ በሥራው ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

የቆዳው ዘርፍ ሰፊ የሰው ኃይል የሚይዝ ዘርፍ ስለሆነ ቀደም ሲል ጀምሮ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶት እየሰራበት ነው የሚሉት አቶ ተስፋዬ፤ አሁንም ከውጭ ለሚመጡት ግብዓቶች ትኩረት ሰጥቶ በደንብ ቢሰራ ከቆዳው ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ እንደሚቻል ይናገራሉ፡፡ ኢትዮጵያ በቆዳ ምርቶቿ በውጭ ሀገር ገበያ ላይ መታወቋ በራሱ ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ቀደም ሲል ቆዳው በጥሬ ሄዶ እነሱ እሴት ጨምረው ለኛ መልሰው የሚሸጡበት ሂደት እንደነበረም ይናገራሉ፡፡ ስለዚህ ቆዳው እሴት ተጨምሮበት በእንደዚህ ዓይነት መልኩ ተሰርቶ ለውጭ ገበያ መቅረቡ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው ተናግረዋል፤ የኢትዮጵያ እድገት አንድ መገለጫ እንደሆነም አንስተዋል፡፡

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ ቀደም ሲል መንግሥት ለቆዳው ዘርፍ የሰጠው ትኩረትና እገዛ አሁንም መቀጠል አለበት፡፡ ድርጅቱ አሁን ላይ ለሃያ አምስት ሠራተኞች የሥራ እድል የፈጠረ ሲሆን፤ አሁን ያለው የሰው ኃይል ምርቶችን ለኤክስፖርት ለማድረግ ብቁ አይደለም፡፡ ይህ ድርጅት በደንብ ወደ ማምረት ሥራው ገብቶ ምርቶቹን ለውጭ ገበያ ማቅረብ ሲጀምር የሚምርተው ምርት መጨመር ስላለበት የሚያስፈልገው የሰው ኃይል መጨመር ይኖርበታል፡፡

ለምሳሌ ድርጅቱ ለውጭ ገበያ 500 ቦርሳዎች ማቅረብ ቢጠበቅበት አሁን ላይ በቀን ከአንድ እስከ አምስት ቦርሳዎች ብቻ ነው የሚሰራው፡፡ ይህን መሥራት አሁን ባለው የሰው ኃይል ብዙ ቀናት ይወስዳል፡፡ ስለዚህ ለብዙ ሰዎች የሥራ እድል ለመፍጠር ያስችላል፡፡

ድርጅቱ አሁን ላይ በሀገር ውስጥ ሁለት መሸጫ ሱቆች ያሉት ሲሆን፤ ተጨማሪ ሱቆች ለመክፈትም አቅዷል፤ ከዚህ በተጨማሪ አሁን ላይ ምርቶቹን የማህበራዊ ሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም በደንብ እያስተዋወቁ እንደሚገኙ ጠቁመዋል፡፡

በቀጣይ እነዚህ የቆዳ ምርቶች ለውጭ ገበያ መላክ ብቻ ሳይሆን ድርጅቱ በዱባይና በአሜሪካ የራሱን ሱቅ የመክፈት እቅድ አለው ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ ምርቶቹን ወደ ውጭ ሀገር በመላክ ተቀባይ እንዲኖረው ብቻ ሳይሆን ራሱ ምርቶቹን ለመሸጥ እንደሚፈልግ አብራርተዋል፡፡

እንደ ሀገር ለቆዳው ዘርፍ አሁን ትኩረት ቢሰጠውና የቆዳ ሀብቱን ተጠቅመን በቆዳ ውጤቶች በተለይ በቦርሳዎች ብንወዳደር ጥሩ እድል እንዳለን ብዙ አመላካቾች ይታያሉ የሚሉት አቶ ተስፋዬ፤ ከዚህም በተጨማሪ የሥራ እድል በመፍጠር ረገድ ብዙ የሰው ኃይል መያዝ የሚያስችል ሁኔታ እንዳለም አመላክተዋል፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## የምላስ ስፖርተኞች

**ተስፋ ፈሩ**

የጤና ባለሙያዎች የምላስ ውጫዊ ክፍልን በመመልከት ብቻ በምላስ ላይ የሚኖር እብጠትን፣ የቀለም ለውጥን እና ነጠብጣብን በማጤን መላ ሰውነታችን ስላለበት የጤና ሁኔታ ፍንጭ ማግኘት እንደሚቻል ይገልጻሉ፡፡ የሚገርመው ነገር ምላስ ሲንቀሳቀስም በተመሳሳይ መልኩ የአእምሮን ጤንነት መጠቆሙ ነው፡፡ ለዚህም አይደል “አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል” የሚባለው፡፡ የምላስን ኃያልነት የሚገልፁ ብዙ ብሂሎች መጥቀስ ይቻላል፡፡ አሁን ስማቸውን የማላስታውሳቸው አንድ እውቅ ማሲንቆ ተጫዋች ድምጻዊ እንዲህ ተቀኝተዋል፡-

**መቆየት ደግ ነው አየን ብዙ መላ ፤**
**እጅ ሳያቀብል በምላስ ሲበላ፡፡**
**ወጥ በከሰል በእንጨት እየተቀቀለ ፤**
**እንጀራ ባቋራጭ በምላስ በሰለ፡፡**

ሐሙስ የካቲት 30 ቀን 2015 ዓ.ም የታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ገጽ 10 እና 11 ላይ ሁለት የተለያዩ ጽሑፎችን ይዞ ወጥቷል፡፡ ሁለቱም ጽሑፎች ሙሉ ገጽ የሚሸፍኑ ናቸው፡፡ ገጽ 10 ላይ ያለው ጽሑፍ 65 አራት ነጥቦችን ይዟል፡፡ ገጽ 11 ላይ የሚገኘው ጽሑፍ ግን ምንም ዓይነት አራት ነጥብ የለውም፡፡ በአራት ነጥብ መቋጨት የነበረባቸው በርካታ ዓረፍተ ነገሮች እንዲሁ የገጹ ሜዳ ላይ ተበትነዋል፡፡ ሁለቱ ጽሑፎች ባስመዘገቡት አራት ነጥብ ሲወዳደሩ ገጽ 10 ገጽ 11ን 65 ለዜሮ ይመራዋል፡፡ አጋጣሚው መረጃው በሌለን እና በማናውቀው ጉዳይ ላይ በእርግጠኝነት የመናገር ድፍረታችንን እንዲሁም ንግግርን የማንዛዛት ልማዳችንን (አራት ነጥብን የሙጥኝ እንደምንለው እና ምን ያህል እንደምንሸሸው) ለማሳየት የሚያስችል ጥሩ ምሳሌ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

አብዛኞቻችን እያንዳንዱን ንግግራችንን በፍጹም እርግጠኝነት ለመቋጨት ያለን ድፍረት ለአራት ነጥብ ያለንን ፍቅር የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡ ንግግራችንን በ12 ቁጥር ሚስማር እየቸነከርን የአቋም መግለጫ የምናደርገውን ቤት ይቁጠረን፡፡ ሃሳብ “ነው” እና “ናቸው” በሚሉ ድምዳሚ ቃላት ብቻ ሳይሆን ይመስለኛል፤ አስባለሁ፤ እረዳለሁ፤ እገምታለሁ፤ እጠብቃለሁ በማለት አሊያም በጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገርም ይገለጻል፡፡ እነዚህን ቃላት መጠቀም ትህትና የተመላ ግብረገባዊ አቀራረብ ከመሆኑ ባሻገር ድፍረት ከሚጭረው የአንደበት እሳት ይጠብቃል፡፡

አራት ነጥብ የናፈቀው የጋዜጣው ገጽ ደግሞ ንግግርን ቶሎ መቋጨት የማይሆንልንን ሰዎች ይወክላል፡፡ በተለያዩ የውይይት መድረኮች ላይ ዕድል አግኝተው መናገር የጀመሩ ሰዎች ማይክ እንዲለቁ መመኘት የታዳሚዎች ዘወትራዊ እጣ ሆኗል፡፡ በተለያዩ ማህበራዊ ድረገጾችም ያለውን ሁኔታ የታዘበ ሰው መሰል ትዝብት ይገበያል፡፡ በምላስ ወለምታ የምንመታው በዚህ ልማዳችን ሳይሆን አይቀርም፡፡

ንግግርን መግቢያ፣ ዋና አካል (ሐተታ) እና ማጠቃለያ በሚሉ ሶስት ክፍሎች ከፍሎ ማደራጀት ተገቢ እንደሆነ የመስኩ ባለሙያዎች ይመክራሉ፡፡ መግቢያ አጠቃላይ ለንግግሩ ከተመደበው ጊዜ 10 በመቶ፣ ዋናው ንግግር 70 በመቶ ማጠቃለያው ደግሞ 20 በመቶ ሊመደብለት እንደሚገባ ይገለጻል። የኛ ንግግር ባህል ግን እንደ ኮንደሚኒየም ቤቶቻችን 10/90 አሊያም 20/80 ባስ ሲልም 40/60 ነው፡፡ አብዛኞቻችን መግባትና መውጣት እንጂ ማጠቃለል ብሎ ነገር የምናውቅ አይመስለኝም። ገባ ሲባል የሚወጣውን፤ ሀተታ ሲባል የሚፎትተውን፤ ቋጨ ሲባል የሚቀጥለውን ጆሮ ይቁጠረው።

በዓለማችን ረጅም ንግግር በማድረግ ሪከርድ የያዙት የኩባው መሪ ፊደል ካስትሮ ናቸው። መቼም ከእኛ መካከል ይህን ሪከርድ አልፎ ሂያጅ የሚጠፋ አይመስለኝም፡፡ የዘርፉ ጠበብቶች እንደሚገልጹት ከመናገራችን በፊት የምንናገረው ለምንድን ነው ? መረጃ ለማስተላለፍ ወይስ ታሪክ ለመንገር ? ለማሳመን ወይስ ለማዝናናት ? በቅድሚያ ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጠት ይጠበቅብናል፡ ፡ ቀጥሎ የሚከተለው ምን እንናገራልን የሚለው ጥያቄ ይሆናል፡ ፡ የምንናገረው ነገር መረጃ ፣ ታሪክ ፣ ማስረጃ ወይስ አዝናኝ ጉዳይ ነው ? እነዚህ ጥያቄዎችም መልስ ማግኘት አለባቸው።

በየመድረኩና በየአጋጣሚው ሁሉ መናገር ደግሞ ግድ አይደለም፡፡ አንዱ መናጢ ደሃ እጮኛው ቤተሰብ ጋር ሽማግሌ ይልካል፡፡ በቤተሰቦቿ ወገን የተቀመጡ ሽማግሌዎች “ለመሆኑ ምን አለው?” ብለው ሲጠይቁ የወንዱ ወገን ሽማግሌዎች “ሌላ የማጨት አማራጭ” ብለው መለሱላቸው፡፡ ምን ለማለት ነው... ሰው ሃሳቡን የመግለጽ ብቻ ሳይሆን ዝም የማለት ምርጫም አለው፡፡

ዘመናችን የሚፈልገው ንግግር አርቃቂዎችንና በቃላት ተራቃቂዎችን ሳይሆን የተግባር ሰዎችን ነው፡፡ በወሬና ቃል በመግባት ተወዳዳሪ ለማይገኝለት፣ በተግባር ግን ዜሮ ለሆነ ልጃቸው “የምላስ ስፖርተኛ” የሚል ቅጽል ስም ያወጡ እናት አውቃለሁ፡፡ ማህበረሰባችን እያሌ የምላስ ስፖርተኞች አቅፏል። የሚሰለጥንባትና እናሰልጥንህ የሚሉት እነሱ ናቸው፡፡ አንዲት የተግባር ቅንጣት ሳናይ በንግግር ብቻ የምንጠግብ ብዙዎች ነን፡፡ ፈጣሪ ይመስገን የምላስ ስፖርተኞችን አደብ ግዙ ያለ ከያኒ አላጣንም፡፡ እውቁ የሙዚቃ አቀናባሪ እንዲሁም የዜማና ግጥም ደራሲ ኤሊያስ መልካ በድምጻዊ ኢዮብ መኮንን አንደበት እንደሚከተለው ይህን ማህበረሰባዊ ህጸጻችንን ኮንኖታል፡፡

**ተጠራርተን ከየቤቱ ቃልን መርጠን መሻማቱ፤**
**ለመናገር መጎምጀቱ ለኛስ ነው ወይ መድኃኒቱ፤**
**ለምን አደንቃለሁ ጥሩ ቃል መራጩን፤**
**በምላሱ ስለት የምናብ ቆራጩን፡፡**
**ሁላችን ከሆንን የቋንቋዋ ፈላስፋ፤**
**በተግባር መስካሪ እማኝ እንዳይጠፋ፤**
**አንድም ሳይጨበጥ ሳይዳሰስ እንኳን፤**
**ጀግና ልንባል ነው ቃልን ካሰካካን፡፡**
**አስተዋልኩኝ ብሎ የምሩን ቢነግረኝ፤**
**አሳጨበጭብም መደሃኒት ካልሰጠኝ፤**
**ለፈለፈው እንጂ መች አጣሁት እኔ፤**
**አይራቀቅበኝ እድናለሁ ያኔ፡፡**

እዚህ አንድ ቦታ ያነበብኳትን ጨዋታ ጣል ባደርግ ጥሩ ይሆናል፡፡ አንድ ወጣት አጠገቡ ለነበሩ ሰዎች በጨዋታ መልክ እንዲህ ሲል ጥያቄን አቀረበ “በአንድ መሬት ላይ በተጋደመ ትልቅ ግንድ ላይ ሶስት እንቁራሪቶች በመደዳ ቆመው ነበር፡፡ አንደኛዋ እንቁራሪት ቆመው ከነበረበት ግንድ ላይ ለመዝለል ወሰነች፡፡ ስንት እንቁራሪቶች ቀሩ?” ይህንን ጥያቄ የሰሙት በሙሉ መልሳቸው፣ “ሁለት” የሚል ነበር፡፡ ሰውየውም መልሳቸው ትክክል እንዳልሆነ ገለጻላቸው፡፡ “አንዷ እንቁራሪት የመዝለል ውሳኔ አደረገች እንጂ አልዘለለችም፡፡ ስለዚህ አሁንም የቀሩት ሶስት እንቁራሪቶች ናቸው” ነበር ማብራሪያው፡፡

“አያችሁ”፣ አለ በመቀጠልም፣ “ይህ የሚያመለክተው ውሳኔን ከተግባር ጋር የማምታታት ዝንባሌያችንን ነው፡፡ አንድ ውሳኔ ወደተግባር እስኪለወጥ ድረስ ከውሳኔው በፊት ከነበርንበት ሁኔታና ደረጃ ትንሽም እልፍ አያደርገንም፡፡” አብዛኛውን ጊዜ አንድን ነገር ለማድረግ ከወሰንን በኋላ ልክ እንዳደረገ ሰው ኑሯችንን እንቀጥላለን። ውሳኔ ግን ያው ውሳኔ እንጂ ተግባር ማለት አይደለም።

የምላስ ስፖርተኞች ይወስናሉ እንጂ ተግባሩ ላይ የሉበትም። እነዚህ አካላት በክፋት መስመር ሲሰለፉ የሚያስከትሉት ጥፋት ማጣፊያ የለውም፡፡ በማህበራዊ ሚዲያው በለው... ቁረጠው... ፍለጠው እያሉ ጥላቻን በመስበክና ወንድምን በወንድም ላይ ማስነሳት እሳት የሚያስነሱት የምላስ ስፖርተኞች ናቸው፡፡ ዶክተር በድሉ ዋቅጅራ “ፍካታ ናፋቂዎች” በተሰኘ የግጥም ስብስቦችን በያዘ መጽሐፉ፣ የምላስ ስፖርተኞችን ሚና በሦስት መስመር ስንኞች እንደሚከተለው ምጸታዊ በሆነ መንገድ ገልጾታል፡፡

**ከገለባ ፋም ሸጉጠው፣**
**ሹፍ ብለው አቀጣጥለው፣**
**እሳት ሲያጠፉ እንዲያ ነው፡፡**

በእውቀቱ ስዩም በበኩሉ በአንድ ግጥሙ የምላስ ስፖርተኞችን እንደሚከተለው በሁለት መስመር በግሩም ሁኔታ ገልጿቸዋል፡፡

**ለጀግናው ሐውልት ስሩ ፣ ጀብደኛውን ሸልሙት**
**እኔን ተዉኝ ፣ አንሶላዬ ውስጥ ልሙት፡፡**

የምላስ ስፖርተኞች ያነሳሳሉ፤ ይገፋፋሉ፤ ያሳምጻሉ፤ ያፋጃሉ እንጂ ሜዳው ላይ መገኘት የማይፈልጉ አንሶላ ውስጥ ሟቾች ናቸው፡፡ እንደ ማህበረሰብ እንዴት በምላሳውያን መዳፍ ውስጥ ተገኘን ብዬ ስጠይቅ ነሐሴ 25 ቀን 1592 የተወለደው ኢትዮጵያዊው ፈላስፋ ዘርዓ ያዕቆብ ከ500 ዓመታት በፊት የወረወረውን ሃሳብ እቀልባለሁ፡፡

ዘርዓ ያዕቆብ “ሰዎች ሁሉ ሐሰትን እንጂ እውነትን የማያስተውሉት ለምንድነው? (ምክንያቱ) የሰው ተፈጥሯው ደካማና ስልቹ ስለሆነ መሰለኝ። ሰው እውነትን ይወዳል፤ አጥብቆም ያፈቅራታል። የተፈጥሮን ስውር ነገሮች ማወቅ ይፈልጋል። ግን ነገሩ አስቸጋሪ ነው፤ ያለ ትልቅ ጥረትና ትዕግሥት አይገኝም፤ ሰሎሞን እንዳለው፥ ከፀሐይ በታች ስለተፈጠረው ሁሉ ልቤን ለምርመራና በጥበብ ለመፈተን ሰጠሁ፤ ምክንያቱም ይደክሙበት ዘንድ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ክፉ ድካምን ሰጥቷቸዋል። ስለዚህ ሰዎች መመራመርን አይፈልጉም፤ ከአባቶቻቸው የሰሙትን ያለምርምር ማመንን ይመርጣሉ እንጂ” ይላል።

# ዓለም አቀፍ



## እስራኤል፣ ሀማስ እና አሜሪካ ጊዜያዊ ስምምነት ላይ መድረሳቸው ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

እስራኤል፣ ሀማስ እና አሜሪካ ጊዜያዊ ስምምነት ላይ መድረሳቸው ተገለጸ።

እስራኤል፣ ሀማስ እና አሜሪካ ጦርነቱን በጊዜያዊነት ጋብ ለማድረግ እና በደርዘን የሚቆጠሩ ታጋቾችን ነጻ ለማድረግ ጊዜያዊ የሆነ ስምምነት ላይ መድረሳቸውን ሮይተርስ ዋሽንግተን ፖስትን ጠቅሶ ዘግቧል። ለአምስት ቀናት ተኩሱ ጋብ እንዲል በተደረገው ስምምነት የሚለቀቁት ታጋቾች ህጻናት እና ሴቶች መሆናቸውን ዘገባው ጠቅሷል።

እንደዘገባው ከሆነ ስድስት ገጽ ባለው ስምምነት መሠረት ሁለቱም አካላት ለአምስት ቀናት ውጊያ ሲያቆሙ ቢያንስ 50 የሚሆኑ ታጋቾች በየ24 ሰአቱ በተለያዩ ትናንሽ ቡድኖች ሆነው ይለቀቃሉ። ስምምነቱ ተግባራዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የአየር ላይ ቅኝት እንደሚካሄድም ተገልጿል።

ሀማስ ባለፈው ጥቅምት ወር የእስራኤልን ድንበር በመጣስ እጅግ ከባድ እና ያልተጠበቀ ጥቃት አድርሶ 1200 ሰዎችን ከገደለ እና 240 የሚሆኑትን ካገተ በኋላ እስራኤል በሀማስ ይዞታ በሆነችው ጋዛ ላይ ሙሉ ጦርነት ከፍታለች።

እስራኤል እየወሰደችው ባለው የእግረኛ እና የአየር ጥቃት እስካሁን ከ11 ሺህ በላይ ፍልስጤማውያን መገደላቸውን የጋዛ ባለሥልጣናት ተናግረዋል። የእስራኤል እና ሀማስ ጦርነት ከተቀሰቀሰ ከአራት ሳምንታት በላይ ሆኖታል።

በጋዛ ተኩስ እንዲቆም የሠብዓዊ ድርጅቶች እና በርካታ ሀገራት ቢጠይቁም፣ እስራኤል እና አጋሯ አሜሪካ ሳይቀበሉት ቆይተዋል።

## ዩክሬን የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትሯን ጨምሮ በ108 ግለሰቦች ላይ ማዕቀብ ጣለች

በጋዜጣው ሪፖርተር



ዩክሬን የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትሯን ጨምሮ በ108 ግለሰቦች ላይ ማዕቀብ መጣሏን አስታወቀች፡፡

ዩክሬን በ108 ግለሰቦች እና 37 የሩሲያ ተቋማት ላይ ማዕቀብ የጣለች ሲሆን ማዕቀብ ከተጣለባቸው ሰዎች ውስጥ የዩክሬን የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ማይኮላ አዛሮቭ ይገኙበታል።

ውሳኔው ከዩክሬን ህጻናትን አስገድደው ወደ ሩሲያ ያስገቡ ሰዎችን ተጠያቂ ለማድረግ ያለመ መሆኑን ፕሬዚዳንት ቮልድሚር ዜለንስኪ ተናግረዋል። ፕሬዚዳንቱ ማዕቀብ የተጣለባቸውን ሰዎች በዝርዝር ባይናገሩም ፊርማቸው ያረፈበት ሰነድ በግለሰቦቹ ላይ ከአምስት እስከ 10 ዓመት እስር ቅጣት ባሻገር የሀብት እገዳን ጨምሮ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ማዕቀቦችም ተጥለዋል።

አብዛኞቹ አዲስ ቅጣት የተላለፈባቸው የሩሲያ ዜግነት ያላቸው ሰዎችም ከዚህ ቀደም በተለያዩ ወንጀሎች ተጠርጥረው ቅጣት የተላለፈባቸው መሆናቸውንም ሬውተርስ ዘግቧል።

የቀድሞው የዩክሬን ጠቅላይ ሚኒስትር ማይኮላ አዛሮቭ እና በየካቲት ወር የዩክሬን ዜግነታቸውን የተነጠቁት የቀድሞው የትምህርት ሚኒስትር ዲሚይትሮ ታባቺንክ ቅጣት ከተላለፈባቸው 108 ሰዎች መካከል ናቸው ተብሏል። የክሬሚያ እና ሉሃንስ ግዛት አስተዳዳሪዎችም የተለያዩ ማዕቀቦች ተጥሎባቸዋል የተባለ ሲሆን፥ 37ቱ የሩሲያ ተቋማት ደግሞ በህጻናት ላይ የሚሠሩ መሆናቸው ተገልጿል።

ኬቭ 20 ሺህ የሚጠጉ ዩክሬናውያን ህጻናት ያለወላጆቻቸው ወይም አሳዳጊዎቻቸው ፈቃድ ወደ ሩሲያ እና ሩሲያ ወደተቆጣጠረቻቸው የዩክሬን ግዛቶች ተገደው እንዲገቡ መደረጉን ታምናለች። የአሜሪካው የል ዩኒቨርሲቲ ከቀናት በፊት ባወጣው ጥናትም ከ2 ሺህ 400 በላይ ዩክሬናውያን ህጻናት ወደ ቤላሩስ በሃይል መወሰዳቸውን ይፋ አድርጓል።

የዓለምአቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ዩክሬናውያን ህጻናት ወደ ሩሲያ ተገደው ገብተዋል በሚል በመጋቢት ወር በፕሬዝዳንት ቭላድሚር ፑቲን ላይ የእስር ማዘዣ ማውጣቱ የሚታወስ ነው።

# የባህር በር የአብሮ መሥራት እና የትብብር መንፈስ

**በትረ ሙሴ (መልክ ኢትዮጵ)**

ኢትዮጵያውያን በታሪካቸው ማንንም በድለው አያውቁም፡፡ በመካፈልና ሰጥቶ በመቀበል የምናምን የፍትህና የሚዛናዊነት ልኮች ነን፡፡ በታሪክ ውስጥ የተነሱ ማናቸውንም የወሰንና የይገባኛል ጥያቄዎች አንዱን የበላይ አንዱን የበታች አድርገን አናውቅም፡፡ ሰጥቶ በመቀበል መርህ ውስጥ ሀገርና ሕዝብ የሆንን ነን፡፡

በቀይ ባህር (በወደብ) ጉዳይ ላይ የተነሳው ጥያቄም ይሄን መሰል የጋርዮሽ አንድምታ ያለው ነው፡፡ ምንም እንኳን ተፈጥሮ ለእኛ አድልታ የቀይ ባህርን ታሪክ ከታሪካችን ጋር አስተሳስራናለች። ዛሬም ጥያቄያችን ታሪክ ጠቅሰን ታሪካችንን መልሱልን የማለት አይደለም፡፡ ጎረቤቶቻችንን አስታውሰን የአብሮ ማደግን ጥያቄ ነው ያነሳነው፡፡ ጥያቄው ይሁንታን አግኝቶ ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን ደግሞ ትልቁ መነሻችን ውይይት ሆኖ ከፊት ተቀምጧል፡፡ ውይይት ልዩነቶችን አስታርቆ ወደአንድነት የሚወስድ ሂደት ነው፡፡

እንደ ቀይ ባህር ባሉ ለብዙዎች የሕልውና ጥያቄ በሆነ ጉዳይ ዙሪያ ተወያይቶ እንደመግባባትና ተግባብቶ አብሮ እንደመሥራት የተሻለ መንገድ የለም፡፡ ብዙኃኑን ያቀፈ የሃሳብ ልውውጥ ያስፈልጋል፡ ፡። እንደ ሀገር መነሻችን የይገባኛል ጥያቄ ቢሆንም መድረሻችን ግን አብሮ መሥራት ነው፡፡ በባህል፣ በታሪክና በምጣኔ ሀብት ለተሳሰሩ ሀገራት ከብቻነት ይልቅ የአብሮነት ሃሳብና ተግባራዊነት ነው የሚበጀው። ይሄን መሰሉ አካሄድ ደግሞ ማንንም ሳይበድልና ማንንም በዳይ ሳያደርግ ተያይዞ ማደግን የሚያመጣ ነው፡፡ ዘመኑ ከጦርነት ወደሰላማዊነት የተሸጋገረበት ነው፡፡

የኃይል ርምጃዎች ማንንም ፊተኛ እንዳላደረጉ በደንብ የገባን ጊዜ ላይ ነን፡፡ የትኛውም ፍላጎት፣ የትኛውም ጥያቄ ሰላም ለበስና ምክንያታዊነትን ያስቀደመ እስከሆነ ድረስ በውይይት የማይፈታበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ የባህር በር ጥያቄያችን ከምክንያታዊነትና ከሰላም ናፋቂነት አኳያ ውይይትን መሠረት ማድረጉ ለአብሮነት የሰጠነውን ዋጋ የሚያሳይ ነው፡፡

በተረፈ አፍሪካዊ መልክ ኖሮት በአፍሪካውያን ተጠንቶ እልባት እንዲሰጠው በቀድሞ አካሄዳችን ‹አፍሪካዊ ችግሮችን በአፍሪካዊ መፍትሔ› ልንቃኘው የሚገባ ጭምር ነው፡፡ ፍላጎትን መሠረት ያደረጉ እንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ከአብሮ መሥራት ባለፈ መቀራረብንና መነጋገርን ብሎም አፍሪካዊ እይታዎችን እንድናመነጭ መንገድ የሚጠርጉ ናቸው፡፡

በቀይ ባህር ላይ ኢትዮጵያውያን ያነሳነው ጥያቄ ቀድሞ ሊነሳ የሚገባው እጅግ የዘገየ ቢሆንም ዋናው ነገር ግን የጥያቄው ተገቢነት ነው፡፡ በፖለቲካም ሆነ በዓለም አቀፍ የሚዛናዊነት ንጻሬ ውስጥ እንደትልቅ መመዘኛ ሆኖ የሚታዩት ጉዳዮች አንዱ ሃሳብ ነው፡፡ በሃሳባችን ልክ መሆን በራሱ ትልቅ ስኬት ነው፡፡

ጥያቄያችን በቀይ ባህር፤ የባህር በር ባለቤትነት ላይ የቆየና ታሪክ የሚመሰክረው የባለቤትነት ይዞታ ቢኖረንም፤ በጋራ አስበን፣ በጋራ መክረን በጋራ እንጠቀም የሚል ነው። ይሄ የእኛ የኢትዮጵያውያን ሚዛናዊነትን የተላበሰ ነው እንጂ፤ ታሪካችን በሆነው በዓባይ ወንዝ ላይ አንድ ጭልፋ ውሃ እንዳንጨልፍ ተከልክለን የቆየንበት ጊዜ ነበር፡፡

የባህር በር ጥያቄ የአንድ ፓርቲ ወይም ደግሞ የአንድ የሆነ ቡድን ሃሳብ ሳይሆን የሁላችን የጋራ እውነት ነው፡፡ አቋማችንም የጋራ መሆን አለበት፡፡ አብዛኞቹ ታሪኮቻችን የተወሰዱብን፣ የደበዘዙብንና የተወረሱብን ጉዳዮቻችንን የአንድ የተወሰነ አካል ብቻ ስላደረግናቸው ነው

እኛ የፍትህ ወዞች ነን፡፡ እውነት አፍ ቢኖራት ኢትዮጵያውያንን ቀርባ እንደምታናግር ብዙዎች የመሰከሩልን ማንነታችን ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜ ያነሳናቸው ሕዝባዊ ጥያቄዎች እኛን ብቻ ተጠቃሚ አድርገው ሌላውን እንዲጎዱ የሚፈቅዱ ሳይሆኑ ተያይዘን እንራመድ ዓይነት መልክ ያላቸው ነበሩ፡፡

የሰው የማንፈልግ፣ የራሳችንንም እንዲነኩብን በማይፈቅድ የሉዓላዊነት ጥላ ውስጥ በቅለን የጸደቅን ሕዝቦች ነን፡፡ በፍቅርና በጨዋነት ለመጡብን ብቻ እንድንሸነፍ የሚፈቅድ ተፈጥሮ አለን፡፡ ዓባይና ቀይ ባህር ተፈጥሮ በኢትዮጵያዊነት ላይ ያደራቸው የታሪክና የማንነት ጉምቱ መነሻዎች ናቸው፡፡

የባለቤትነት ጥያቄዎቻችን በጨዋነት ጀምረው በጨዋነት ካበቁ፣ ውይይትና በአብሮ ማደግ መርህ ስር ሰፊ መድረኮችን ማዘጋጀት ከቻልን የባህር በር ጥያቄያችን መልስ የሚያገኝበት ሂደት የተቀላጠፈ ይሆናል የሚል የባለሙያ አስተያየቶች እየተደመጡ ናቸው፡፡ ብዙዎች በታሪኮቻችን ሲያጌጡ ኖረዋል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር በቅርብ ርቀት ላይ ያለች ሀገር ናት፡፡ ይሄ ብቻ አይደለም በስማችንና በታሪካችን ሲጠራ ዘለግ ላሉ እልፍ ዓመታት መቆየቱ ይታወቃል፡፡ ይሄ ሁሉ በሆነበት ምክንያት ውስጥ ግን ወደብ አልባ ሀገር ሆነን ከሶስት አስርት ዓመታት ከራቀ ጊዜ ቆይተናል፡፡

የባህር በር ጥያቄ አሁን ላለውም ሆነ ወደፊት ለሚፈጠረው ትውልድ የሕልውና ጉዳይ ነው። ከኢኮኖሚና ከፖለቲካ፣ ከደህንነትና ከፍላጎት አንጻር ይሄ ነው የማይባል ጥቅም ያለው ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር በሕዝብ እንደራሴዎች ፊት ባሰሙት ንግግር ላይ ሰፋ ያለ ምክንያታዊና ቁጭት ለበስ ሃሳቦችን አንስተው ማወያየታቸው ይታወሳል፡፡

የይገባኛል ጥያቄያችንን ከሕልውና ጥያቄ ጋር አቆራኝተው፣ የማደግ እና የመለወጥ ተስፋችን እውን የሚሆንበት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ቀይ ባህርና ዓባይ ወንዝ ኢትዮጵያን የሚበይኑ፣ ከኢትዮጵያዊነት ጋር የተቆራኙ፣ ለኢትዮጵያ ዕድገትና ጥፋት መሠረት የሚሆኑ በመሆናቸው ከዚህ ርዕስ መሸሽ እንደማያስፈልግ የጠቆሙበትን ሁኔታ ማስታወስ ይገባል፡፡

የወደፊቷን ኢትዮጵያ በሕዝብ ቁጥር አሰፋፈርና በፍላጎት መናር ስንቃኛት የባህር በር እጅግ አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በምሥራቅ አፍሪካና በአፍሪካ መንደር ካለን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጽዕኖ ፈጠሪነት እንዲሁም የሕዝብ ቁጥርን ማዕከል ካደረገ የፍላጎት መጨመር ጋር ተያይዞ አግባብነት ያለው ጥያቄ መሆኑ እውቅና ይሰጠዋል፡፡

አሁን በተነሳው የይገባኛል ጥያቄ መሠረት ሀገራችን የባህር በር ለማግኘት የጋራ ተጠቃሚነትን ባስቀደመ መልኩ ብዙ አማራጮች እንዳሏት በብዙ የዘርፉ ባለሙያዎች ተገልጸዋል። እንደምሳሌ የተነሳው የዘይላ ወደብ ነው፡፡ የዘይላ ወደብ ከመቋዲሾ በብዙ ርቀት ላይ ስላለ ከሶማሊያ ይልቅ ለኢትዮጵያ አመቺ ሁኔታ ያለው ነው፡፡

በዚህም መሠረት ሶማሊያ በኢትዮጵያ በኩል የሚገባትን ጥቅም አግኝታ ኢትዮጵያ ወደቡን እንድትጠቀመው ማድረግ ቀላሉና አዋጩ መንገድ ነው፡፡ ልክ እንደዚህ ሁሉ ከኤርትራ ጋር በተፈጠረው መልካም ጉርብትና የጋራ ተጠቃሚነትን ማዕከል ባደረገ መልኩ የአሰብን ወደብ የምንጠቀምበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይቻላል፡፡

በሕዝብ ቁጥሯ ከአፍሪካ ቀድማ ከዓለም ከቀዳሚዎቹ የምትጠቀስ ሀገር፣ በየጊዜው የሚጨምር የሕዝብ ፍላጎት ባለባት ሀገር ላይ የባህር በር ጥያቄ ጥቅሙና ልክነቱ የማያወላዳ ቢሆንም፤ ሰላም ተኮር በሆነ የውይይት አማራጮችን ማየቱ ደግሞ የበለጠ ነገሩን ተመራጭ ያደርገዋል፡፡

የትኛውም የአብሮ ማደግ ሃሳብ በውይይት/በድርድር ካልሆነ የማይሰምሩ ናቸው፡፡ አሁን ላነሳነው ጥያቄም ሆነ ወደፊት ለምናነሳው ብሔራዊ ጥቅምን ለተንተራሰ ጥያቄ በጋራ ተጠቃሚነት ውስጥ የጋራ ተግባቦት ያለው አካሄድ እጅግ ተመራጭ ነው፡፡

ሰላማዊና ዲፕሎማሲያዊ አካሄዶች ተግባቦትን ለመፍጠር የመጀመሪያዎቹ ምርጫዎች ናቸው፡፡ የጋራ ፍላጎት በጋራ ምክርና ውይይት መልስ የሚያገኝ ነው። በሕዳሴ ግድባችን ላይ ያሳየነውን ሕዝባዊ አንድነትና መነቃቃት በባህር በር ጥያቄያችንም ላይ በመድገም ትንሳኤዎቻችንን ማፍጠን እንችላለን።

የባህር በር ጥያቄ የአንድ ፓርቲ ወይም ደግሞ የአንድ የሆነ ቡድን ሃሳብ ሳይሆን የሁላችን የጋራ እውነት ነው፡፡ አቋማችንም የጋራ መሆን አለበት፡፡ አብዛኞቹ ታሪኮቻችን የተወሰዱብን፣ የደበዘዙብንና የተወረሱብን ጉዳዮቻችንን የአንድ የተወሰነ አካል ብቻ ስላደረግናቸው ነው፡፡

ሌላው ዓለም ስለሀገሩና ስለታሪኩ አንድ ዓይነት አመለካከት ነው ያለው፡፡ እኛ ሀገር ግን ታሪክ ተከፋፍለን የእኔ የአንተ በሚባል ልክፍት ውስጥ ነን፡፡ ይሄ ዓይነቱ የመለያየት አስተሳሰብ ነው የጋራ እውነቶቻችን ላይ መግባባት አሳጥቶ ማንም ጣልቃ ሲገባባቸው ሀይ ባዮች እንዳንሆን ያደረገን፡፡

ዓድዋ የእኛ ነው፡፡ የሕዳሴ ግድባችን የጋራችን ነው፡፡ የቀይ ባህር/የወደብ ጉዳይም የህልውናችን ጉዳይ ነው፡፡ ስንጠይቅም በጋራ፣ ስንመካከርም አብረን መሆን አለበት፡፡ በሀገር ጉዳይ ላይ እኔን አይመለከተኝም በሚል እሳቤ ውስጥ ታሪክ አይፈጠርም፡፡ ታሪክ በራሱ ታሪክ ሰሪ ትውልድን ታኮ የሚመጣ ነው፡፡

ታሪክ ሰሪ ትውልድ ደግሞ አንድነትንና አብሮነትን ተቀብሎ በጋራ ሥርዓት ውስጥ የሚኖር ነው፡፡ የባህር በር ጥያቄም ከዚህ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነው፡፡ ጥያቄው በመንግሥት በኩል ይነሳ እንጂ አጀንዳው ሀገራዊ ነው። ሀገራዊ አጀንዳ ደግሞ ታሪክና ትውልድ የሚፈጥር የብዙኃነት መልክ ነው፡፡

ከዛሬ ወደ ነገ የሚሄድ፣ ታሪክ የሚመልስ፣ ትውልድ የሚያንጽ፣ ፍላጎትን መሻትን የሚያረካ የመኖርና ያለመኖር የሕልውና ጉዳይ ነው። ተባብረንና ተጋግዘን አብሮ ማሰብ ስንችል ነው መሰል ጥያቄዎቻችን ፍሬ አፍርተው የሚታዩት። በሀገር ጉዳይ ላይ የግለሰብ ወይም ደግሞ የፓርቲ ጥያቄ የለም፡፡ ሁላችንም ስለሆነውና ስለሚሆነው የሚያገባን ነን፡፡

በውይይት/በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ጥያቄዎቻችን መልስ አግኝተው የባህር በር ባለቤት እንደምንሆን ተስፋ አለን።

ተስፋዎቻችን ወደመሆን እንዲመጡ ደግሞ ሰላም ያለበት፣ ምክክር የቀደመበት አፍሪካዊ ሃሳብና መድረክ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የዲፕሎማሲ ሥራ የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል፡፡ በዘርፉ ልምድና ተሞክሮ ያላቸው ተናግረው ማሳመን የሚችሉ፣ ለመግባባት ቅርብ የሆኑ አካላት ያስፈልጉናል፤ አበቃሁ፡፡

# ስፖርት





## ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ለ23ኛ ጊዜ በድምቀት ተካሄደ

**ብርሃን ፈይሳ**

ከሁለት አስርተ ዓመታት በላይ በርካታ ቁጥር ያላቸው ተሳታፊዎችን በማወዳደር ተወዳጅነትን ያተረፈው የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ትናንት ለ23ኛ ጊዜ በድምቀት ተከናውኗል። ኢትዮጵያውያን እንዲሁም የጎረቤት ሀገራት አትሌቶችን፣ ኤምባሲዎችንና የውጭ ሀገር ዜጎችን እንዲሁም ሌሎች 45ሺ ተሳታፊዎች እንደወትሮው ሁሉ የ 10 ኪሎ ሜትር ውድድሩን አድምቀውታል። መነሻውንና መድረሻውን መስቀል አደባባይ ያደረገው የ 10 ኪሎ ሜትር ዓለም አቀፍ የጎዳና ላይ ሩጫ በበርካታ ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሃንም ሽፋን አግኝቷል።

‹‹ክትባት ለሁሉም ህጻናት›› በሚል መሪ ሃሳብ የተካሄደውን ይህን ውድድር የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ እንዲሁም የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ አስጀምረዋል። በኦሊምፒክና ሌሎች ዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ውድድሮች ላይ በረጅም ርቀት የተደጋጋሚ ክብር ባለቤቷ ደቡብ አፍሪካዊት የቀድሞ አትሌት ኤላና ሜየር እንዲሁም ታዋቂው የአትሌቲክስ ጋዜጠኛ ቲም ሃቺንግስ በክብር እንግድነት የተገኙ ሲሆን፤ ኢትዮጵያን በተለያዩ ውድድሮች ማስጠራት የቻሉ አንጋፋና ወጣት አትሌቶችም በመድረኩ ተሳታፊዎች ሆነዋል።

የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ መስራች ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴን ጨምሮ በርካታ የኦሊምፒክ፣ የዓለም ቻምፒዮና እንዲሁም ሌሎች ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ስኬታማ የሆኑ አትሌቶች በዚህ መድረክ የተገኙ ሲሆን በርካታ አርቲስቶችና ስመጥር ሰዎችም ተሳታፊዎች ነበሩ። 500 የሚሆኑ አትሌቶች (በሴት 200 እንዲሁም በወንድ 300) በሁለቱም ጾታዎች የተለያዩ ክለቦችን ወክለው እንዲሁም በግላቸው ተሳትፈዋል። ደመናማ የአየር ሁኔታ





በሪሁን ታደሰ

**ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በ45ሺ ተሳታፊዎች ታጅቦ ለ23ኛ ጊዜ በድምቀት ተካሂዷል፣**

በነበረው ውድድር ወጣትና ልምድ ያላቸው አትሌቶች ጠንካራ ፉክክር ማድረግ ችለዋል። በውጤቱም በወንዶች የኢትዮ ኤሌክትሪክ አትሌት የሆነው ወጣቱ አትሌት ቢንያም መሃሪ አሸናፊ ሆኗል። በግሉ የተሳተፈው ዘነበ አየለ እና የኮዬ ፈጩ ክፍለከተማ አትሌቱ ጂራታ ሌሊሳ ደግሞ ተከትለውት ገብተዋል።

በሴቶች በኩል የኢትዮጵያ ንግድ ባንኮቹ አትሌቶች መልክናት ውዱ እና ተኪና አማረ አንደኛ እና ሶስተኛ ደረጃን በመያዝ ሲያጠናቅቁ ሌላኛዋ አትሌት መገርቱ አለሙ ከኤሊት አትሌትስ ሁለተኛ ሆና ማጠናቀቅ ችላለች። የአሸናፊዎቹ አትሌቶችም የዋንጫ ሽልማትን ጨምሮ የ200 ሺ፣ 100 ሺ እና 50ሺ ብር ተሸላሚዎች ሆነዋል። ከሩጫው በኋላም በወንዶች አሸናፊ የሆነው ወጣቱ አትሌት ቢንያም፤ በውድድሩ እንዲሁም በአሸናፊነቱ ደስተኛ መሆኑን ገልጿል። የአጭር ጊዜ ልምምድ በማድረግ ወደ ውድድር በመግባት የነበረውን ፈታኝ ፉክክር አልፎ አሸናፊ እንደሆነም ባለድሉ አትሌት ተናግሯል። አትሌቱ ልምምዱን በአዲስ አበባ ማድረግ ከጀመረ አንድ ዓመት ያስቆጠረ ቢሆንም ከዚህ ቀደም በተካሄደው የኢትዮጵያ ቻምፒዮና ተሳታፊ በመሆን ሁለተኛ ደረጃን መያዝ ችሎ ነበር። በቀጣይም ከሀገር ውስጥ ውድድሮች ባለፈ ሀገር በምትወከልባቸው ውድድሮች ተሳትፎ ስሟን በኩራት ለማስጠራት አቅዶ በመሥራት ላይ መሆኑንም ጠቁሟል።

አምና በታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ሶስተኛ ደረጃን ይዛ ማጠናቀቅ የቻለችው አትሌት መልክናት ውዱ ዘንድሮ ድል ቀንቷታል። በዓመቱ ዳይመንድ ሊግን ጨምሮ በበርካታ ውድድሮች ላይ ተሳታፊ የነበረችው መልክናት የአየር ሁኔታው ሩጫውን ከባድ ቢያደርገውም ፈተናውን ተቋቁማ አሸናፊ ልትሆን እንደቻለች ተናግራለች። ከዚህ በኋላም ትኩረቷን በቀጣይ ውድድሮች ላይ በማድረግ ውጤታማ የመሆን ጥረቷን እንደምትቀጥል አብራርታለች።

ጀግናው አትሌትና የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ መስራች ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ፤ ሩጫው በየዓመቱ እያደገ 23ኛው ላይ ሲደርስ በ45ሺ ተሳታፊዎች መካሄዱን ገልጿል። የውድድሩን ጥራት በመጨመርም ዓለም አቀፋዊ ይዘቱን ለማሳደግ እንደተቻለ የተናገረው ኃይሌ፣ ይህንንም በዓለም አቀፍ ደረጃ የጎዳና ላይ ሩጫ አዘጋጆች መለኪያ 98 ከመቶ ውጤት የተሰጠው መሆኑን ማረጋገጥ እንደተቻለ ጠቁሟል። በዚህ ውድድር ተሳታፊ የሆኑ አትሌቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ ውድድሮች ተፈላጊ ናቸው፤ በመሆኑም በርካታ ማናጀሮች ተገኝተው ይመለከታሉ። ይህም የሆነው ከአዲስ አበባ የቦታ አቀማመጥ አኳያ በሩጫው መሳተፍ ጥንካሬን ስለሚጠይቅ ነው። በመሆኑም በውድድሩ አሸናፊ የሚሆኑ አትሌቶች የሚያገኙትን ሽልማት በ30 ከመቶ ማሳደጉን አንጋፋው አትሌት ያስረዳል።

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ 10 ኪሎ ሜትር እየሸፈነ ላለፉት 23 ዓመታት የተካሄደ ውድድር ሲሆን፤ ከዚህ በኋላ ግን ከዚህ ያለፈ እንዲሆን እየታሰበ መሆኑን ኃይሌ ይጠቁማል። የዓለም አትሌቲክስ ከሚመራቸው ውድድሮች መካከል አንዱን (ሀገር አቋራጭ፣ የወጣቶች ቻምፒዮና፣...) ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት ጥረት በመደረግ ላይ እንደሚገኝም አክሏል።